
# የኔዎቹ ገረዶች



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# የኔዎቹ ገረዶች

ከጳውሎስ ኞኞ

## ማውጫ

ምዕራፍ ፩6

ምዕራፍ ፪11

ምዕራፍ ፫15

ምዕራፍ ፬20

ምዕራፍ ፭24

ምዕራፍ ፮34

ምዕራፍ ፯39

ምዕራፍ ፰44

ስለደራሲው በጥቂቱ51

የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች።

፪ ተሰሎንቄ ፫/፲፯

ይቺን መጽሐፌን ደግሞ አቀርብኩላችሁ፤ ስለ ገረዶች ታወራለች፤ አወራርዋ እንደ ገረዶች በመሆኑ ምናልባት ለተራቃቂው አንባቢ አትጥመው ይሆን ይሆናል።

እግዚአብሔር ሰው አድርጎኝ ተቀጥሬ ለገረድ መቅጠር ከበቃሁበት ጊዜ ጀምሮ የቀጠርኳቸው ገረዶች ሁሉ አብሽቀውኛል፤ አንዲቱም በሰላም ከቤቴ አልሔደችም፤ ሰድበውኝ፤ አታለውኝ፤ አናደውኝ፤ ሔደዋል። እንደመልካቸው ብዛት ጠባያቸው ያንኑ ያህል ሆኖብኛል። ወይም ደግሞ አብሻቂው ፍጥረት እኔው ራሴ እሆን ይሆናል፤

የምታውቁት እንደምታውቁት ሁሉ ደራሲ ለመባል ወይም ደግሞ ከደራሲዎች ደረጃ መጽሐፍ የምጽፍ አይደለሁም። ከልጅነቴ ጀምሮ ደብዳቤ መፃፍ እወድ ነበር ያው ልምድ ሆኖብኝ አሁንም መሞጫጨር እወዳለሁ።

የምሞጫጭረው መሞጫጨር ሳላስበው አንድ አጭር ታሪክ ቢጤ ይፈጥርልኛል፤ አንድ ላይ ሳጋጨው አንድ መጽሐፍ ቢጤ ይሆናል፤ ይታተማሉ ብትወዱም ባትወዱም ከገበታችሁ ላይ አቀርበዋለሁ።

እኔን የሚያደክመኝ ይሔን ብል እንዲ ብለው ይተረጉሙብኛል፤ በዚያኛው ዓይነት አጻጻፍ ብመራት የፈተናውን ቦታ አትወጣውም፤ ያን የፈተና ተራራ ወጥታስ ለአንባቢ የምትደርሰው በምንኛው ቀላል አጻጻፍ ነው? የሚለው ሐሳብ ነው።

ስለዚህ ነው በየእንቧጮውና በየቀጨሞው የአጻጻፌን ዓላማ የምመራው፤ የመርማሪው ጓድ በተሰጠው የመጻሕፍት መመርመሪያ ደንብ ሾኬዋን (ደስታ) ከትቦ ካልወጣላት ማንኛይቱም መጽሐፍ ካለችበት መቆም አለባት። አማሮች «ሁሉን ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል» ይላሉ።

«የኔዎቹ ገረዶች» መጽሐፌ ቡዝም የምታስደስት አይመስለኝም ያን ብልም «ቂጥኝን መጫወት ከወርዶ ጋር ነው» እንደሚባለው በገረድ የተገሩ የስምንተኛው ሺህ ሰዎች ቁስላቸውን ትነካቸው ይሆናል አንድ የገረድ አምጪዬ የሆኑት ባልቴት «በስምንተኛው ሺህ ቀጣሪም ተቀጣሪም ወፈፌዎች ናቸው፤ መቻቻል ነው» ብለውኛል። ደግሞም «በስምንተኛው ሺህ ሰው በረከሰበት፤

እኔውም እብድ አንቺን ያመንኩበት» የሚለውን ግጥም አዝማሪዎች ሁሉ ይጠቀሙበታል። እኔም እናንተም እንግዲህ የስምንተኛው ሺ ሰዎች ነን።

ነቃዎች ሞልተዋል፤ አመስጋኞችም ብዙዎች ናቸው፤ ሁሉን አጠቃሎ ማስደሰት አይቻልም፤ እግዚአብሔር አላደረገውም፤ በተለይም ባገራችን ልቅ ነን የሚሉ በሞሉበት ባሁኑ ዘመን በነቃፊዎች አንደበት መነቀፋ እምብዛም አያስደነግጥም።

ሁሉም ይሁን፤ አረረም መረረም «የኔዎቹ ገረዶች» አቀረብኩላችሁ፤ ልብ ወለድ ናት፤ የምታስፈልጋችሁ ቢሆን አንብቧት፤ ባትወዷት ከመጽሐፍ ማኖሪያ ዘረንጋችሁ አኑርዋት።

ደህና እንሁን

# ምዕራፍ ፩

«በሥራዬ በጠባዬ የታወቅሁ ነኝ፤ ስለ ጠባዬ ማንም ይመሰክራል» አለችኝ በመዝጊያው አጠገብ ቆማ በእግርዋ ጣት ሳንቃውን እያሻሸች።

ከፎቴዬ ላይ ተቀምጬ እጆቼን ግራና ቀኝ ከደፎቹ ላይ አድርጌ «ታዲያ ለጊዜው አሥራ አምስት ብር ይሁንልሽ፤ ባይሆን ሥራሽ እየታየ ይጨመርልሻል» ብላት ካቀረቀረችበት ቀና ብላ «ስለ ሥራዬ ወለቱም ታውቃሉ» ብላ መልሳ አቀረቀረችና «ከሃያ ብር ወርጄም አላውቅም» አለችኝ።

እንደዚያው እንደነበርኩበት ሁኔታዬ ሆኜ »በሥራሽ ካስደሰተሽኝ ሃያ ብር ሩቅ አይደለም» ብላት እንዳቀርቀረች ጣቶችዋን በጣቶችዋ እያፍተለተለች «በፊት እኮ ደመወዜ ሐያ አምስት ብር ነበረ፤ እንዴት አሥር ብር ልቀንስ» አለች።

ወደ እመት ወለቱ ዞር አልኩና «አይ እንግዲህ» ብዬ ስጀምርላቸው አቋረጡኝና ወዳመጧት ገረድ ዞር ብለው «አይ እንግዲህ ትገቢ እንደሁ ግቢ፤ ባታይው ነው እንጂ እሱ ልጅዬ አስተካክልሽልኝ አይበለኝና ልክ እንደ ቅዱስ ሚካኤል ደግ ነው፤ ቤቱም ይሔው እንደምታይው ነው አሽከሩና እሱ ብቻ ናቸው፤ በነገራችን ላይ፤ ያቺ አበበች ካንተ ቤት በመውጣቷ እስታሁን ታለቅሳለች፤ ጠግባ የወጣችው፤ ደሞ ላንተ ቤት፤ አሁንም አንቺ ጣጣ አታብዢ፤ አርፈሽ ግቢና ጓዳሽን ተረከቢ፤ ገንዝበ ምንድን ነው? ዋ ኧረ ሰው ይበልጣል ነጭናጫ ሆኖ መቶ ብር ምንሽ ነው? ዋናው ዓመል ነው፤ አንቺም ደህና ልጅ ነሽ፤ ዓመልሽን አሳምረሽ ተቀመጪ ደስ ካሰኘሽው እንኳ ሃያ ብር ሐያ አምስትም አይቆጨው፤ ሠላሳስ ቢሆን ደግሞ ለሱ ደግነት ዋ እቴ ጎረቤት ይመስክር፤ የሁሉ ኪስ ነው፤ አሁንም አርፈሽ በይ በዚያው እሱ ባለሽ በአሥራ አምስት ብር ግቢ «ብለው ቢቆጧት አንገትዋን እንደ ደፋች ቀስ ብላ» እሺ እርሶ ካሉ» አለች።

አገጬን ይዤ የእመት ወለቱን ንግግር ካዳመጥኩ በኋላ አገጬን ለቅቄ ተዝናናሁና «አዎ ሁሉም ይደርስበታል፤ ለመሆኑ ጠላ መጥመቅ ታ» ብዬ

ሳልጨርስ እመት ወለቱ ጣልቃ ገቡና ወደ እመጡዋት ገረድ ትኩር ብለው እያዩ «አዎ ቤቱ የእንግዳ ቤት ነው እሱም ቢሆን እንደ ዘመኑ ልጆች ሳይሆን ጠላ ይወዳልና ኩስትር የዶሮ ዓይን የመሰለ ጠላ እየጠመቅሽ ማቆየት አለብሽ» አሏት።

አዲሲቱ ገድ ሳቅ ብላ ወደ እመት ወለቱ እያየች፤ «ለሱስ ግድ የለም፤ ምነው እማማ ወለቱ ያውቁት የለም እንዴ? » ብትላቸው እመት ወለቱ እተቀመጠበት ፎቴይ ላይ ቆነጥነጥ በልው ወደዳርዋ ወጥተው ተቀመጡና «ለካ እቴ ለካ፤ አውቀዋለሁ» አሉና ፊታቸውን ወደኔ ዞር አርገው «በዚህ ሐሳብ አይግባህ፤ ቁንዶ ናት» አሉኝ።

አሁንም እንደ በፊቱ ሁኔታዬ ሆኜ «አዎ ደሞ ዋናው ነገር ወጥ» ብዬ ስጀምር እመት ወለቱ አቋረጡኝና «እንዴታ፤ ነው እንጂ በፊትም፤ ነገሬሻለሁ፤ ቆፍጣና ነው፤ እንዲህ አይምሰልሽ ቅድም ስንመጣም ነግሬሻለሁ፤ ያቺ ገረድህ ማነው እቴ ስሟ - ካለ ጠባይዋ ሁሉ ወጥ አታበስልም ነበር፤ እይው እሱ ኩስትር ያለች ወጥ ዓይነቷ በርከት ያለች - ሆድ የለው - ምን ሆድ አለውና - ዋቴ ቢበላ ኖሮ መች እንዲህ ይሆን ነበር። - ዋ - ብቻ ያቺው ክትን ጥፍጥ ብስል ብላ እንደትቀርበልት ያስፈልጋል» አሏትና ወደኔ ዘወር ብለው «ለዚህ እንኳ ልጅቱ ሞያ አላት» አሉኝና እንደ ገና ወደ ገረዲቱ ዞር ብለው «እይው ብቻ እሱ እንደ ዘመኑ ልጆች አይደለምና ይኸን ባስታሹጣ ነው ምንድነው እምትሉት አይወድም» አሏት።

በእመት ወለቱ ንግግር መሐል ጣልቃ ገብቼ «አዎ ቢሆንም አዩት አንዳንዴ» ስል እመት ወለቱ አቋረጡኝና «እሱማ ነው፤ ላይነት - ምግብ አልበላ ሲልማ ይደረጋል፤ ብቻ ሸንኩርቱም ቅመሙም ሳይበዛ ጭዋንም በልኳ አድርጐ ይሠራል - አይ ልጅቱ እንኳ በዚህ ሞያ አላት ቅመም ናት» አሉኝ።

የእመት ወለቱ ጣልቃ መግባት ቢያስከፋኝም ቢያስደስተኝም ከገረድ ጋር ያለንን ውል ለማስተካከል ወደ ኋላዬ ለጠጥ ብዬ ከፎቴው ተደገፍኩና «አዎ ደሞ ዋናው ነገር ፅዳት ብዬ ስጀምር ገና ሳልጨርሰው እመት ወለቱ

አሁንም አቋረጡኝና «ነው እንጂ - ይሔንንማ እሷስ ሙች አጣችው» አሉኝና ወደ ገረዲቱ ዞር ብለው «እዩው እሱ ንጹሕ ነው፤ ንፅሕና ይወዳል፤ ጥርግ ጥርግርግ መሬቷን ውልውል፤ አሽከሩን መቆጣጠር ጉድፍድፉን ሁሉ ብድግድግ እንዲያው ሣር - ሣር አልኩሽ ጠብ ብትል ብድግ» አሉዋትና ወደኔ ዘወር ብለው «ልጅቷ እንኳ በዚህ በኩል እውቅ ሹር ነች፤ አታየውም ልብሷን፤ ንጽሕናስ እሷም ትወዳለች ትእዛዝም አትሻ» አሉኝ።

የእመት ወልቱ ጣልቃ መግባት ጊዜ ቢወስድም ከአዲሲቱ ገረዴ ጋር የግድ የወደፊት የኑሮአችንን ሁኔታ መነጋገር ስላለብኝ እንደ ገና ደሞ «ደሞ ዋንው እንገር የመንደር ወሬ» ብዬ ሳልጨርሰው እመት ወለቱ አቋረጡኝና «የምን ወሬ - ወሬቱ - ወሬስ እንዲያውም አልወድ - ኧረ አልወድም እዩው ይሔ የመንደር ሴት መገናኘት - እንዴ ከፉ ነው፤ እሳት እንጭራለን ብለው ይመጣሉ፤ ሰፌድ፤ ሙቀጫ፤ ወንፊት አውሱኝ ብለው ይጠቻሉ፤ ለሰበብ እኮ ነው እዩው አንቺም እንዲያው ምን ልበልሽ - እንዲያው አንዲት ሴት ወር ትልና - አንቺም እቤትሽ ቁጭ - እንዲይው ብቅ ትይና - ያው ገበያ ብቻ ትሔጃለሽ - ከዚያ እቤትሽ ከትት - ደሞ ወሬ - የምን ወሬ እቴ» አሏትና ወደኔ ዞር ብለው «አይ ለዚህስ ልጅቱ ምሥጉን ነች ጭምት ነች» አሉ።

ገረዲቱም ፈገግ ብላ «ዋ - ሁሉንስ እማማ ወለቱ ያውቁት» ብላ ሳትጨርስ እመት ወለቱ አቋረጧትና «እንዴታ በሚገባ ነው - አውቃታለሁ - ቢሆንም እኔንም እንዳታሳፍሪኝ - አውቄሽማ ነው እጨዋ ቤት ያገባሁት፤ እኔም እጨዋ ቤት ገብቻለሁ፤ እንዳታሳፍሪኝ አደራ፤ እሱ እንደሁ ልጃችን ነው፤ የኛው ነው፤ ዋ ዛሬ ስታይው ትልቅ ሽማግሌ ይምስልሽ እንጂ ምናለውና ነው? እርምታህል ነው - እኛ እናውቀዋለን፤ እንግዲህ ደሞዝሽ በአቦ ይታሰብልሻል» አሉና ብድግ ሲሉ እኔም ልሸኛቸው ብነሳ «ተቀመጥ እኔ ጓዳውን ላሳያት ብለው ይዘዋት ገቡ።»

ከዚያም ሲመለሱ ተሰናብተውኝ ሲሔዱ ገረዲቱ ልትሸኛቸው ብትል «የምን መሸኘት - በኔው ጀምሪ 0 በይ ቅሪ - አሮጊት ልጅ ነገር ያመጣል» አሉና መለሷት።

ገረዲቱም ስትመለስ «ስምሽ ማነው እቱ» ብላት እየተቅለሰለሰች ቆም አለችና «አበበች ነው» ብላኝ ወደ ጓዳ ገባች።

የመድኃኔ ዓለም ዕለት ከደብደን ለምሳ ጋበዝኩትና እቤት ሔደን ላንድ እኩል ሰዓት ይህል ከእልፍኝ ተቀምጠን ስንጫወት ቆየን፤ የምግብ ቤቱ ጠረጴዛ አልተሠራም፤ ገረዶችን ተቆጣጥሮ ማዘዙ እረፍት ስለሚመስለኝ ዝም ብዬ ተበቅን።

በኋላ የመጥሪያ ደወል ብደውል የሚመጣ ጠፋ፤ ተነስቼ አበበችን ስጣራ ከውጪ መጣች፤ «ምነው ምሳ አታቀርቢም? » ብላት እሺ ብላኝ ገባ እንደ ነገሩ በልተን ተጋባዡ ሳይደሰት ሔደ።

ማታ ካልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ መጽሐፍ ሳነብ አበበች ከመኝታ ቤት በር ላይ ቆመችና «የሥጋ መግዣ» አለችኝ።

«ጥዋት የሰጥሁሽስ»

«ሠራሁታ»

«የአምስት ብር ሥጋ? »

«አይ አይደለም»

«ታዲያስ»

«ግማሹን ነው»

«ግማሹስ»

«ውሻ ወሰደው»

«የማ ውሻ»

«የአባ ጆቢር»

«በየት ገባ»

«በበሩ»

«ለምን አልዘጋሺውም»

«እትዬ አምሳለ ቤት ሔጄ ነው»

«ለምን ሔድሽ»

«ሰፌድ ልዋስ»

«የኛስ ሰፌድ»

«ለእትዬ አልማዝ አውሼ ነው»

«አውሰሽ ልትዋሽ? »

«አዎ»

«ከውጭ ላትዞሪ ውል አልነበረንም? »

«ታዲያ እኔ ምንላድርግ»

«እንዴት»

«ከሰው ሳልገናኝ እሠራለሁ - ኦ ኦ ኦ»

«ምን ያገናኝሻል»

«አይ እኔ እናትዬ ነገር አልችልም፤ ቢስጡኝ ስጡኝ፤ ባይሰጡኝ እኔ ከየት አምጥቼ እሠራለሁ፤ ጆሮዬን አልጨምርበት፤ እጄን ቆርጬ አልሠራውም አለችና ትመልሳ ስትሔድ «እንዴት ዓይነቱ ቤት ገባሁ እቴ» አለች።

ወር ከአሥራ አምስት ቀናት ያህል ከቤቴ እንደኖረች እሁድ ዕለት ጥዋት ከመኝታ ቤቴ መጥታ ከበራፉ ላይ ቆማ «ዛሬ ፈቃድ ይስጡኝ» አለችኝ፤ «እንግዶች ይመጣሉና ነገ ትሔጃለሽ» ብላት «አይ እኔ ወንድሜ ታሞብኛልና እሔዳለሁ ጠይቄው እመጣለሁ» አለችኝ አይሆንም አልኳትና እያጉረመረመች ካጠገቤ ሔደች።

ከሲኒማ ቤት ዋልኩና ማታ ከቤቴ የጋበዝኳቸው እንግዶች ስለ ነበሩ በአሥራ ሁለት ሰዓት ከቤቴ ገባሁ፤ ዝግጅቱን ልጠይቅ አበበችን ብጣራ አሽከሬ ከበደ ምነው ጥዋት ሔዳ አለኝ።

# ምዕራፍ ፪

ደላላው ወርቁ ገረድ እንዲያመጣልኝ ነገርኩት፤ የሻነሽን ይዞልኝ መጣ፤ የድካሙንም ዋጋ ሁለት ብር ሰጥቼው ሔደ።

የሻነሽን በቀጠርኳት በሦስተኛው ዕለት ማታ እራቴን በልቼ ከዚያው ከምግብ ቤት እንደ ተቀመጥሁ ከመዝጊያው አጠገብ ፊትዋን ዞራ የቆመችውን ገረዴን ከዚህ በፊት ከየት ነበርሽ? ብላት መሬቱን እያየች ካንድ ትልቅ ሰው ቤት ነበርኩ አለችኝ።

«ለምን ወጣሽ? » ብላት «መቼም መልከ ቀና መሆን መጥፎ ነገር ነው» አለችኝ።

«ማነች እምልከ ቀናዋ? »

«እነኢው ነኛ እሷማ ጉምድምድ ያለች ናት»

«ማነች ጐመድማዳዋ? »

«ያቺው የቀጠረችኝ ሴትዮ»

«ታዲያ ምን አጣላችሁ»

«ቀናችብኝ»

«ለምን? »

«እንግዲህ ባልየው ዓይናቸው አያርፍም፤ ቅልብልብ ናቸው፤ ታዲያ በቃ ሚስትየዋ ታንቄ እሞታለሁ አለች፤ ሰውዬው ደግሞ በኔ የሙጥኝ አሉ፤ አንድ ቀን ድብልቅልቅ ብለው ሲጣሉ ሴቲዬይቱ ሒጂ፤ ወንድየው አትሔድም እያሉ ሲፋጁብኝ ጊዜ አይ እኔናቴ የሰው ትዳር አላፈርስም ብዬ ወጣሁ።

«መቼም ሴትይቱ ዋና የአህያ ውሀ ጠጪ ናት ስንቱን ጒረምሶች ይዛለች ሰዓት እስኪደርስ ድረስ የትም ስትዞር ትውልና በዓት ብቅ ትላለች፤ የማቀርብላቸው ሽሮ ነበር፤ ኡ እንዲያው ያስኮንናሉ እሳቸው ደግሞ ግድ የላቸውም፤ የሰጧቸውን በልተው ዝም ነው፤ አፈር ይብላኝ።

«በስማምቴ - አንዴ ከወንድ ጋር ስትጫወት እሳቸው ቢመጡ ዕቃ ቤት ውስጥ አስገብታ ቆእለችበት፤ ከእሷስ የኪዎስኮቹ ይሻላሉ፤ ሰውዬው የእግዚአብሔር ሰው ናቸው፤ ታዲያ ሁልጊዜ እቆጭ እናደድ ነበር፤ ምን ያደርጋል በወንድ ልጅ መጫወት - ጡር ነው፤ እግዜርም አይወደው፤ ይጥላል» እያለች ስታወራልኝ፤ ደከመኝና ልተኛ ወደ መኝታ ቤቴ ሄድሁ።

አንድ ቀን ጥዋት ወደ ሥራዬ ልሄድ ስነሳ የሻነሽ ከኋላዬ ተከተለችኝና «ሽሮውም አልቋል» አለችኝ «ስንት ይበቃሻል» ብላት «በርበሬም በቤቱ የለ» አለችኝ ከእልፍኝ ባለው መስተዋት እያየሁ ከረባቴን እያስተካከልሁ «እኮ ለሁሉም ታዲያ ምን ያህል ይበቃሻል» ብላት «የዱቄቱም ዕቃ ባዶ ነው፤ በቤትዋ ያለችው የተቦካችው ብቻናት» አለችኝ።

ወደሱ ዘወር አልኩ ና «እንዴ ምነው ይሄ ሁሉ ጣጣ በቀደም ተገዝቶ አልነበረም ከምኔው አለቀ? » ብላት «እጅዎ ይጣለኝ - ከቤቱ ምንም የለ እየገዛች ለጒረምሳ አብልታ ይሆናል፤ የዛሬ ገረዶች ምስጦች ናቸው ወይም ቀነጫጭባ ገዝታ ይሆናል፤ አፈር ይብላኝ የወንድ ነገር - እርሶማ ምኑን ያውቁታል» ስትለኝ «አይ አንቺም ጨዋ ከሆንሽ ጥሩ ነው፤ በይ አሁን ስንት ልስጥሽ ብላት» «ሃምሳ ብር ይበቃኛል» አለችኝ።

ግንባሬን ኵስትር አድርጌ ዓይን ዓይንዋን እያየሁ «ሃምሳ ብር? » ብላት መሬት መሬቱን እያየች «አብቃቃታለሁ» አለችኝ፤ ፈገግ አልኩና «እኔ እኮ የምልሽ በዛ ነው» ብላት «አፈር ይብላኝ - አይ ጌታዬ ምን አላት መሰሎት? ጣጣው ስንት መሰሎት» አለችኝ፤ እኔም ወደ ሥራዬ ልሄድ ከበርዋ ላይ ስደርስ «ታዲያ ልጅዬ በየሶስት ቀን ሃምሳ ብር አውጥቼ የምዘልቅ ይመስልሻል? » አልኩና ለሳሳ ብር አውጥቼ ብሰጣ እያቅማማች ተቀበለችኝ።

በማግሥቱ «እባክዎ ፈቃድ ይስጡኝ» አለችኝ «ለምን? » ብላት «ከነበርኩበት ቤት ስወጣ ደመወዜን አልተቀበልኩምና ተቀብዬ ልምጣ» አለችኝ ፈቀድኩላት፤ ቀን ለምሳ ስመጣ አዲስ ቀሚስ ለብሳ አየኋት፤ ምሳ ስበላ «ዛሬ ይቅርታ ያድርጉልኝ ያን ደሞዜን እንደተቀበልኩ ይቺን ቀሚስ ልገዛ ብዬ መርካቶ ስለቆየሁ ምሳዎን በደንብ አላዘጋጀሁም» አለችኝ፤ «ግድ የእልም እንዳይደገም፤ እንጂ የዛሬውስ አንዴ ሆኗል» አልኳት።

አንድ ስምንት ቀናት ያህል እንደ ቆየን ጧት ወደ ሥራዬ ልሄድ ስል ከኋላዬ እየተከተለች «የቤት ወጪ ያስፈልገኝ ነበር» አለችኝ፤ ዞር አልኩና «በቀደም የሰጠሁሽስ» ብላት «እኔም ይሄን እንደሚሉኝ እየፈራሁ ነው የጠየኮት - ዛሬ እናትዬ ገበያው ውድ ሆኗል ሁለት ራስ ሽንኩርት ናት በአሥር ሣንቲም የሚሸጡት - ያንለታም ቢሆን ገንዘቡ አንሶኝ ስለ ነበር አብቃቃኋት እንጂ እንደ ልቤ አልገዛሁም» አለችኝ።

ሆቴል መብላትን እንደ ነውር ስለምቆጥረው አሁንም እንደ ገና «ስንት ይበቃሻል» አልኳት ከፊት አቀርቅራ ቆማ «ይሄ ቁጥ ቁጡ እርባናም የለው፤ አንዱን ሳይዙት ያልቃል እኔንም እጀ ሰባራ ያድርጋል፤ አንዴ ሰጥተውኝ አንዴ ብገዛዛና ጓዳውን ብሞላው ይሻላል» አለችኝ።

እንደ ገና ወደ መኝታ ቤቴ ተመልሼ ሄድኩና «ሰባ ብር እሰጥሻለሁ፤ ሁለተኛ ያለ ወር እንዳትጠይቂኝ» አልኳት እያቅማማች እጅ ነስታ ተቀበለችኝ በሦስተኛው ቀን «ፈቃድ ይስጡም» አለችኝ «የት ትሔጅ? » ብላት «በፊት ከነበርኩበት ቤት ደሞዜን ልቀበል» አለችም።

«ምነው በቀደም ተቀብዬ መጣሁ አልላሽኝም።»

«እሱማ አዎ»

«ታዲያስ፤»

«ዛሬ ደግሞ ከፊታውራሪ ቤት ነዋ።»

«ለምን ሳትቀበይ መጣሽ? »

«እኔ ለገንዘብ ግድ የለኝም፤ ለጊዜው ይነደኝና እወጣና ለሁም ጋ በኋላ ነው የምቀበለው»

«ሌላ ብዙ አትሔጅምና ዛሬ ጣጣሽን ጨርሰሽ እንድትመጪ» ብያት ሄድሁ በሰዓት ስመጣ የለችም፤ ማታ ስመለስ ከቤት አገኘኋት፤ «ምነው ቀን የት ጠፋሽ ምሳስ ለምን አላዘጋጀሽም ነበር? » ብላት «እንዲያው ጌታዬ እኔም ሳዝን ነው የዋልኩት - ደሞዜን ተቀበልኩና ገንዘቧ ሳትጠፋብኝ ካንድ ነገር ላይ ላውላት ብዬ ከመርካቶ ሔጄ አንድ ያበሻ ቀሚስ ገዛሁና ሳሰፋ ሰዓት አለፈብኝ» አለችኝ፤ «ሁለተኛ እንዳይለምድሽ» ብያት እራቴን በልቼ ተኛሁ።

በሦስተኛው ቀን እሑድ ጧት እያለቃቀሰች መጣችና ከመኝታ ቤቴ በር ላይ ቆመች፤ እንደ ተኛሁ «ምን ሆንሽ ብላት «እኅቴ ታማ በነፍስዋ ድረሺ የሚል መልእክት ደረሰኝ» አለችኝ፤ «ማን አመጣልሽ» ብላት እያለቃቀሰች ንፍጥዋን እየጠራረገች «ጧት የኛ ሠፈር ሰው መጥጦ ነበር፤ እርሶ ተኝተው ስላረፈዱ ቸኩሎ ሔደ እኔም ሳላስፈቅዶት አልሄድም ብዬ ከጧት ጀምሬ እንዳለቀስኩ ነኝ» አለችኝ።

«አሁን ታዲያ ምን ትፈልጊያለሽ» ብላት «እንዲያው ሳትሞት የኅቴን ዓይን ልያት ብዬ ነው፤ የዛሬን አዳሬን ፈቃድ ይስጡኝ» አለች፤ እኔም በለቅሶዋና በሁኔታዋ ደንግጬ ነበርና ሁለት ብር ከራስጌ ኮመዲኖ ላይ አንሥቼ ሰጠኋትና «በይ ሂጂ እስቲ እግዚአብሔር ይማርልሽ» አልኳት።

እሑድ የሄደች ሮብ ድረስ ሳትመጣ ቀረች፤ ዓርብ ዐልት ካቶ ጅማ ቤት ለቅሶ ለመድረስ ጣልያን ሠፈር ከሚባለው አምባ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገዳማ ስናፍል ባንዲት ኪዎስክ ውስጥ ቀይ መብራት በርቶ ካልጋዋ አጠገብ ካለች አንዲት የእንጨት ወንበር ላይ ቁጭ ብላ ኮቴ ስታዳምጥ የሻነሽን አየኋት።

# ምዕራፍ ፫

ቂን ቂን ማለትዋን ንጽሕናዋ እሰው ፊት ብትቀርብም የማታሳፍር ስለ ሆነች በየወሩ አሥራ አምስት ብር ልከፍላት ቀጠርኳት፤ ወርቂቱ አፍንጫዋ ጐመድ ያለ ቢሆንም ቅብርብር ያለች መግላሊት ቢጤ ደስ የምትል ጐማዳ የገረድ አማሪነት ነች።

ጥሩ ስትሰራ ከረመች፤ በሥራዋም አስደሰተችኝ። ገረዶች ሲለዋወጡ፤ በወረት በአፍላው በአዲስነታቸው ቅንብርብር አድርገው ይሠራሉ። ብዙ ትእዛዝ አይፈልጉም፤ ለሁሉም ነገር አዋቂ ሆነው ይገኛሉ፤ መስለው መታየትንም ይወዳሉ።

ወርቂቱ በቤት አያያዝዋና በወጥ ቤት ሥራዋ አንዱን ወር ሙሉ ደስ አሰኘች፤ የመጀመሪያ ወር ደሞዝዋን ስከፍላት ሁለት ብር ጨምሬ ሰጠኋት፤ ሁለቱ ብር በጉርሻ መልክ ነው።

በወር ከአሥራ አምስት ቀንዋ ገደም «ሴት ሆኜ ሴትን ማየት ደስ አይለኝም» አለችኝ፤ ሳቅ አልኩና ያቀረበችልኝን ሻይ ፉት ብዬ «ለምን? » ብላት «አልወድም፤ ሴት ካለችበት ቤት የማልቀጠረውም በዚሁ ነው፤ ጌቶች እንኳ ሃያ አምስት ብር አደርግልሻለሁ ሲሉኝ እንቢ ብዬ ወጣሁት በዚሁ ነው፤ ሚስትዮዋ እንኳ ከኔ የማትሻል ውዳቂ ሆና ተመስገን ብላ እንደ ሙብላት ትቀናባቸዋለች፤ ሰውዬው ደግሞ ይገርሞታል ያላንቺ ሌላ ሴት የታለና ብለው ድርቅ አሉብኝ፤ እንጃ እንዲያው ከዕድሌ ነው መሰለኝ ወንዶቹ ሁሉ ድርቅ ይሉብኛል» አለችና እንደመሽኮመም ብላ አቀርቅራ አየችኝ።

የቁርስ ዳቦዬን ጉርሼ እያላመጥሁ «ነውር አይደለም እንዴ! እንዴት የቀጠረችሽን የመቤትሽን ባል ትነጥቂያለሽ? » ብላት ቆጣ ብላ ግንባርዋን ኮስትራ ቀና ብላ አየችኝና «እ! ደሞ እሷ ብሎ እመቤት! እባክዎ እቴ ጊዜ ጥሎን ነው እንጂ እኛም እመቤት ነበርን! «ስትለኝ፤ አቋረጥኳትና «ቀጥረሽ ታሠሪ ነበር እንጄ? » «አልኳት»

«መቅጠር ምን ዋጋ አለው፤ ጊዜ ነው፤ ቤቶቼ ስንት አሽከር ነበራቸው አሉ፤ እኔስ ብሆን መቼ እንዲህ ወድቄ እቀር ነበር፤ አመል ነስቶኝ ነው እንጂ አባቴ ለአገር አበዳሪ ናቸው፤ የሳቸውን እንጀራ የማይበላ የለም፤ አዎ ብቻ ምስክር በሌለበት ቢያወሩት ሁሉም ውሸት ይመስላል፤ እየመጡስ ይጠይቁኝ የለ - ባይሆን እንደ ሴቶቹ እንኳ ነግጂ ብለው የስጡኝን ገንዘብ ለማይረብ አጠፋሁት፤ አጉል ባልንጀራ ምን ያረጋል ገደል ይሰዳል በኔ ገንዘብ እንኳ ዛሬ ስንቶቹ ናቸው ጌታ የሆኑት - አንድ ለማጣ የሆነ ሰው ወዳጅነት ያዝኩና መቼም ወንዱ ሁሉ እኔ አላቅም አበድኩ ነው የሚለኝ ይሄንኑ ዕድል ብሎልኝ ነው መሰለኝ፤ እሱ ነው ለዚህ ያበቃኝ» አለችኝ።

ነገር ብቀጥል በወሬ ከሥራዬ እንደምታስቀረኝ ስላወቅሁ ኮቴን ለብሼ ወደ ሥራዬ ሄሁ፤ በምሳ ሰዓት ጥሩ ምግብ አዘጋጅታ ቆየችኝ፤ ደስ እንዲላት ብዬ «ጥሩ ምግብ ነው ያዘጋጀሽው? » ብላት ቀለስለስ ብላ እየተሽኮረመመች «ዋ! ለሞያውማ - እኔ አልነበርኩም ወይ ምንትሱ አለች አለ ሴትይዮዋ - እባክዎ እቴ ጊዜ ጥሎን ነው ለግርድና የበቃነው!» አለችና የበላሁበትን ሰሃን አነሳስታ ሄደች።

ማታ ስገባ አጋጊጣ ከእልፍኝ ተቀምጣ አገኘኋት ከወገብና ካንገትዋ ተውነጥንጣ «ኖሮ እንኳን ደህና መጡ» አለችና ብድግ ብላ ቆመች፤ «በግዜር እሜቴ ይቀመጡ» አልኳትና በእጄ የያዝኩትን መጽሐፍ እንደያዝሁ ቁጭ ብዬ ማንበብ ስጀምር እጫማዬ ድረስ ተጠግታ ከፊት ለፊቴ ቆመችና እየተውረገረገች «ሻይ ወይስ ቡና» አለችኝ፤ «ይቆይ» አልኳት፤ እንደ ገና ደግማ «ጠላ ወይስ ጠጅ አለችኝ፤ ከፎቴው ላይ ጋደም እንዳልኩ በማነባት መጽሐፍ አናት ላይ እየኋትና «ጠጅ ጠምቀሻል እንዴ» ብላት «ብገዛሎትስ» አለችኝ።

መጽሐፌን እያየሁ የማነብ መስዬ «ገንዘብ ከየት አገኘሽ? » ብላት እንደ መጀመሪያ ሁኔታዋ ከቆመችበት እየተውረገረገች «ለእርሶ ሕይወቴንስ ቢሆን - ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ተብሏል - የሚሉኝን ሁሉ ልፈጽም ዝግጁ ነኝ፤ እርሶ ያለብዎት ማዘዝ ነው፤ እኔ ያለብኝ እሺ ማለት ነው፤ ይዘዙኝ፤ ልታዘዝ» አለችኝ።

ነገርና ሁኔታዋ ቢገባኝም እንዳልገባኝ መስዬ «ቆይ አሁን መጽሐፍ ማንበብ ይዣለሁ» ብላት «ሲጨርሱ እታዘዛለሁ» ብላ ወደ ጓዳ ገባች፤ ምን ላንብብ ከምን ልድረስ አላውቀው አንብቤ እየጨረስሁ ገጾችን እገለብጣለሁ፤ ምን እንዳነበብሁ አላውቅም፤ መጽሐፊቱም ምን እንደምትል አልገባኝም፤ ዓይኔ ፊደላቱን ይቆጥርል፤ ልቤ ስለ ወርቂቱ ሁኔታና አባባል ያውጠነጥናል፤ አንዳንዴ እናደዳለሁ፤ አንዳንዴም እገረማለሁ፤ ለምን ተደፍሬም እላለሁ፤ መጽሐፊቱን አንብብቤ እመጨረሻይቱ ገጽ ደረስሁ፤ ለመጨረሻ ጊዜ የመሐፊቱን የመጨረሻ ወፍራም ሽፋን ገልብጬ ስከድናት አስደንጋጭ መብረቅ ጮሆ ዝናቡ ከበፊቱ ጨምሮ በኃይል መዝነም ጀመረ።

እራቴን ስበላ አንድ ጠርሙስ ሳባ ጠጅ አቀረበችልኝ፤ «ለምን ገዛሽ?» ብላት «ምነው ጠላ ይጠጡ የለ እንዴ» አለችኝ፤ «ጠላ እጠጣለሁ ግን ጠጅና አረቄ አልጠጣም» አልኳት።

ከቀዳችለት ብርጭቆ ላይ ወደ እጅዋ አፍስሳ ከእፍኝዋ ቀመሰችና «ዛሬ ይቺን ባይጠጡ ጠብ ነው፤ እኔ ለርሶ ብዬ ካለችኝ ገዝቼ መጠጣት አለቦት፤ ፈጽሞ አይቀርም አለችኝ፤ ለጊዜው እንደመናደድም እንደመደሰትም አደረገኝና ከመኝታ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ፤ ወርቂቱ የመኝታ ቤቴን በር ከፍታ ገባችና ቆመች፤ ምነው? ብላት «እግርዎን እንዳጥብ ብዬ ነበር» አለችኝ፤ «አልታጠብም» አልኳትና ቅር እያላት ወጣች፤ እኔም መጽሐፍ አነብ ጀመር።

ጥቂት ቆይታ እንደ ገና ተመልሳ መጣችና አሁንም ከመሐል ሜዳ ቆመች፤ ዓይኔን ከማነበው መጽሐፍ ላይ ላላነሳ ምነው? ብላት «የነገ ወጪ እንዲሰጡኝ ብዬ ነበር» አለችኝ፤ «የነገውን ነገ ጠይቂኝ» ብላት አሁንም ቅር እያላት እያዘገመች ስትወጣ በሩን ሳትዘጋው ሄደች።

እንደ ገና ደግሞ ጥቂት ቆይታ ተመልሳ መጣችና በፊት ከቆመችበት ቦታ ቆመች፤ አሁንም ዓይኔን ከማነበው መጽሐፍ ላይ ሳላነሳ እንደ በፊቱ ሆኜ ምነው አልኳት፤ «ተልኬ ነው» አለችኝ፤ የማነባትን መጽሐፍ ከዓይኔ ላይ አንስቼ ወርቂቱን እያየሁ «ማን ላከሽ? » ብላት «አቶ አበበ ናቸው»

አለችኝ፤ ከወገቤ ቀና አልኩና «መጥቷል እንዴ» ብላት «አዎ ቀን መጥተው ነበር» አለችኝ።

ተመልሼ ተኛሁና መጽሐፌን ለማንበብ ጀምሬ «ምን አለሽ» ብላት «ዛሬ አይመቸኝም፤ ጧት እመጣለሁ ብለው ነው የሄዱት» አለችኝ፤ «ደህና ነው» ብዬአት መጽሐፌን ማንበብ ስጀምር «የከሰል እሳት ላምጣሎት? » አለችኝ፤ ቀና ብዬ አየኋትና «ለምን» ብላት «እንዴ በዚህ ክረምት በዚህ በሰፊ ቤት ብቻዎን ሲያድሩ ይበርዶታል» አለችኝ፤ ከቤቴ የገቡት ገረዶች ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ነገር በየነበሩበት ቤት የደረሰባቸውን ታሪክ ሲያወሩ እሰማ ነበርና ይህቺም በየደረሰችበት የኔን ስም ታጠፋለች ብዬ አሰብኩ።

ዓይኔን ከመጽሐፌ ላይ ሳላነሳ «አይበርደኝም፤ ለምጀዋለሁ፤ ይልቅስ መዝጊያውን ዝጊልኝና ሄደሽ ተኚ» ብላት በቁጣ አረማመድ እየተራመደች ስትወጣ መዝጊያውን በኃይል ዘጋችው፤ ከቆየን ዘንዳ ሌላ ነገር እንዳይከተል ስለ ሰጋሁ በሬን ቆልፌ ተኛሁ።

ጧት ከመኝታዬ ተነስቼ የለሊቱን ልብሴን እንደ ለበስሁ ስወጣ ከመኝታ ቤት በራፍ ላይ አገኘኋት ገና ስታየኝ ግንባርዋን ኩስትርትር አደረገችና «ደሞዜን» አለችኝ፤ ቆም አልኩና ትኩር ብዬ እያየኋት «የምን ደሞዝ» ብላት «የሠራሁበትን» አለችኝ።

እኔም ተወት አድርጌያት ወደ ፊት እየሄድሁ «ወርሽ ገና ነው፤ የምከፍልሽ ወር ሲሞላ ነው» ብላት ፊትዋን ወደ እኔው አዞራ ከእግር እስከ ራሴ ገላምጣ አይታኝ «አይ እኔ ይከፍሉኝ እንደሆነ ይክፈሉኝ» አለችኝ።

ከምሄድበት ቆም አልኩና መለስ ብዬ «እንዴ ምን ሆንሽና ነው» ብላት በክፉ አስተያየት እያየችኝ «እሱን እንኳ ይተውት» አለች።

«ምን አደረኩሽ»

«እባክዎቴ እሱን አያንሱት»

«ምን ተነካሽ»

«አሁን ጭቅጭቅ ብናበዛ ምን ያደርጋል፤ ብቻ ስጡኝና ልሂድ።»

«እንግዲያስ ደሞዜን ስቀእብል እከፍልሻለሁ።»

«አይ ጌታዬ ብንጣላ ምን ያደርጋል፤ ይልቅ ይስጡኝ»

«የለኝም»

«አሎት»

«አይ እንግዲህ የለም ብየሻለሁና የለም»

«እሱን ይተውትና ይክፈሉኝ እሄዳለሁ»

«ሂጂያ»

«ክፈሉኛ የድህ ጉልበት ምን ያረጋል»

«ለምን ትሔጃለሽ»

«በቃኝ»

«ለምን»

«በቃኝ»

«ምን ተበደልሽ? »

«ማ ከማን ያንሳል - እባክዎን ያናግሩኝ»

«ንገሪኝ»

«እሄዳለሁ፤ ባዩት እቴ ስንቱ ነው የሚያባብለኝ»

«እኔ ምን በደልኩሽ? »

«እባክዎ እቴ ማን ከማን ያንሳል»

«ምን አደረኩሽ? »

«ምነው ጣጣ ባናበዛ እባክዎት ከስንቱ ጋር ነበርን? »

«ሁሉም ይሆናልና በይ አርፈሽ ሥራሽን ሥሪ»

«ምን ያደርጋል አጉል ሐተታ»

«አይ እንግዲህ ነግሬሻለሁ፤ አርፈሽ ሥራሽን ሥሪ» ብዬ በቁጣ ስናገራ ተሽኰርምማ ፈገግ አለችና ሆሆይ ብላ ወደ ሥራዋ ሄደች። የቀን ወጪ ይስጡኝ ብላኝም አስምት ብር ሰጠኋት።

ምሳዬንም እራቴም በጥሩ ሁኔታ በላሁ፤ ማታ የሌሊት ግብዣ ስለ ነበረብኝ ከግብዣዬ ቦታ ሄጄ ስጫወት ነጋ፤ በማግሥቱም ከዚያው ካደርኩበት ቁርሴን ቀምሼ ወደ ሥራዬ ሄድሁ፡

ለምሳ ከቤቴ ብሄድ ቤቱ ጭር ብሎ ዕቃው ሁሉ ተተረማምሶ አገኘሁት፤ ብጣራ የለችም፤ ጓዳ ብገባ በሜዳው ላይ ሹሮው፤ በርበሬው፤ ዱቄቱ ሁሉ ፈስሶ አየሁት፤ የዕቃ ማስቀመጫውን ቁም ሣጥን ብከፍተው ሁሉም ተሟጧል፤ ተግዟል የለም።

# ምዕራፍ ፬

«ይኸን ከመንደር ሴቶች ጋር የያዝሺውን የቡና ማኅበርተኛነት ተይ አይሆንም ያጣላናል» ብላት ተዋበች ከግድግዳው ማዕዘን መሐል ተወሽቃ «ታዲያ እንዴት ላድርግ እነሱ ሲጠሩኝ መቼስ እንቢ አልል» አለችኝ።

ከዚያችው እልፍኝ ፎቴዬ ላይ እግሬን አጣምሬ እንደ ተቀመጥሁ «ግርግዳው በጣትሽ አትሸላልሚው እጅሽ ጥላት እንዳለበት ግርግዳው ይቆሸሻል በቡና ወንፈል ብዙ ነገር እንደሚመጣ አንቺም ያላየሽውን ያልሰማሽውን እያወራሽ ነገር ይመጣልና፤ ስላት አቋረጠችኝና እጅዋን በእጅዋ እያፍተለተለች፤ «እነሱ ናቸው እንጂ እኔ እንዲያውም አላወራቸውም» አለችኝ።

«ምን ይሻላል? »

«እትዬ ጥሩነሽ ሁኔ የምታወራው ስለ ባሏ ነው»

«ምን እያለች»

«እሱ የትም ሲተፋ እያደረ እኔን ችጋር ፈጅኝ በሁለት በሦስትቅ እን አንድ ብር ይጥልልኛል፤ ደግሞ ይግረምሽ ይልና ማታ ማታ እየሰከረ ይደልዘኛል፤ ያንቺን መንቃራ ወፍ እግር ከወሸመ ወዲህ እሷም እንዳቅሚ ስወጣና ስገባ ባግቦ ትሰድበኛለሽ፤ እኔ እንኳ» ብላ ሳትጨርስ አቋረጥኳትና «የት ነች መንቃራዋ? » ብላት «ይቺ ከነሱ ቤት በላይ ያለችው ባለኪዎስኳ» አለችኝ። «እኔ አላአውቃትም? » ብላት «ምነው በቀደም እንኳ እርሶ ሲያልፉ ውሃ ልትረጭቦት እግዜር አወጣኝ አላለቾትም? » አለችኝ።

«እኔ አላውቃትም» ብላት

«እርሶስ ያውቋታል» አለችኝ

«የማወቁ ነገር ይቆይና ታዲያስ? » ብላት «እንዲሁ እያልን ነው የምናወራው - ብቻ ሁልጊዜ ያንቺ ጌታ ደግ ናቸው ይሉኛል፤ ጓዳሽ የሞላ ነው አይቸግርሽም፤ እግዜር መርቆሻል፤ አንቺም ደግ ሰው ብትሆኝ ነው እሳቸው ላይ የጣለሽ፤ ይሉኛል፤ ጌታሽ እንዲህ እያማሩ ጨዋ ናቸው፤ ምነው ለኛ ባሎች ከእሳቸው ጠባይ ጥቂት ባደላቸው? ይላሉ እንጂ እንዲያውም ሰው አናማም» አለችኝ።

«ጥሩነሽስ ቢሆን ባሏን ማንሳትዋ ስለሱ መጥፎ ሥራ ማውራትዋ ማማትዋ አይደለም? » ብላት «እሱ ሐሚታ አይደለም፤ ሁሉም ያወራሉ፤ እትዬ ቆንጂትም ያወራሉ፤ ባሌ ያቺን ቋንጣ በባልዋ ላይ መያዙን ሰማሁና እኔ ደግሞ ባሏን ጠበስኩላት ቢሉ እትዬ ዘቢደሩ ያን አስቀያሚ እንዴት አርገሽ እቴ ቢሏቸው እኔ ምን ቸገረኝ ቁጭቴን ልወጣ እንጂ፤ እሱስ ቢሆን ያቺን አመድማዶ ደረቅ አይደለ የያዘው ሲሉ ጊዜ እትዬ ጥሩነሽ እንዴት አርገሽ አገኘሽው ልጅዬ፤ እሱ ሰው አያናግር ቢሏቸው አይምሰላችሁ ያህያ ውሀ ጠጪ ነው፤ ቀስ እያልሁ በፈገግታ ሳግባባው ጊዜ ደብሪቱን ላከብኝ፤ እኔም ለመግደርደር አይሆንም ሰው ይሰማብናል ብዬ ላክሁበት፤ በኋላ አንድ ቀን ተገናኘንና እራሱ በቃሉ ቢጠይቀኝ ጠበስኩታ አሉን» አለችኝ።

«እንግዲያው ልጅዬ ይህን ሁሉ ከማን ቤት ነው የምታወሩት? » ብላት «ከሁሉም ቤት ነው» አለችኝ።

«ምሳ ምን ጊዜ ትሠራላችሁ? » ብላት «ምን እንዴ ይደርሳል፤ እትዬ ሙላቷ እንኳ ከትናት ወዲያ ባላቸው የመታቸው ምሳ ሳይሥሩ ቀርተው ነው፤ እሳቸውም አበዙት፤ በስማም እቴ - እንዴት ልወንድ ልጅ አይታሰብም? ጋሽ ለማ ያንድ ብር ጠጅ ቢገዛ እሱን ሲጠጡ ሰዓት ደርሶባቸው ነው» አለችኝ።

«አንቺ ያለሽው ከዚህ፤ የባልየውን ማናደድስ የሳቸውንስ መናደድ ምን ታውቂያለሽ? » ብላት «እሳቸው ናቸው ያወሩልኝ» አለች፤ «ምን ብለው» ብላት «በቀደም ለታ ሁለት መቶ ብር በሎተሪ ቢደርሳቸው ሻሽ እንኳ ሳይገዙላቸው አጨበጨቡበት አሉ፤ ደሞ ለሳቸው ሞያ» ብላ ሳትጨርስ «በይ ይብቃን» አልኳትና ተነስቼ ወደ መኝታ ቤቴ ስሄድ «ለመሆኑ አንቺስ ምን እያልሽ ነው ስለኛ የምታወሪላቸው? » አልኳት።

ከወደ ኋላዬ እየተከተለችኝ «ለእርስዎ ደግሞ ምን ይወጣሎታል፤ ያው እነሱም ደግ ኖት ነው የሚሉት፤ እኔ የነገርኳቸውን ይዘው ነው፤ ደሞ ለእርሶ ደግነ» አለችኝ ቆም አልኩና መለስ ብዬ «እንዴት ነው ስለኔ ደግነት የምታወሪላቸው» አልኳትና ከመኝታዬ ቤት ስገባ ከኋላ እየተከተልችኝ የመኝታ ቤቱን በር ደገፍ አለችና «ወጪ እንደ ልብ ይሰቱኛል፤ መቆጣጠር የሚባል ነገር አያውቁም እንደፈለግሁ በባላና ብጠጣ ግድ የላቸውም ቤቱን በሙሉ ለኔው ለቀውልኛል፤ ይውዱኛል» ስትል አቋረጥኳትና «እንዴ በምን ዓይነት መውደድ ነው የምትነግሪያቸው? » ብላት በመሽኮርመም እየተቅለሰለሰች ሳቅ አለች፤ «በይ በቃ ሂጂ» አልኳትና ወደ ሥራዋ ሄደች።

እሑድ እዚያ ይልማ ሠርግ ላይ ብዙ አመሽሁና ሰኞ ከሥራ ብገባ እንቅልፉም ራስ ምታቱም ተደራርቦ አላሠራ አለኝ፤ ወደ ቤቴ ሄጄ ልተኛ አልኩና ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ወደ ቤቴ ሄድሁ፤ በድንገተኛ ከቤቴ ዘው ብል በክፍሉ ያሉት ፎቴዎች ጠበው ግማሾቹ ከመሬት ተቀምጠዋል።

እንደ ገባሁ ሁሉም ደነገጠ፤ ግማሿ ሲኒውን ግማሿ ብርጭቆውን አንዳንዶቹም በእጃቸው የያዙትን ሰሐን እየያዙ ቆሙ፤ ተዋበች ከመሐል ሜዳ ተንዘራፍጣ እንደ ተቀመጠች ፈጥና አነሳለሁ ስትል ከትሪው ላይ ያሉትን ሲኒዎች ብትንትናቸውን አወጣቻቸው።

ለሁለት ደቂቃዎች ያህል መግቢያ አጥቼ ቆምኩ፤ ሽብሩ ሲረጋጋና ስላች መንገድ ስትገኝ በየሥሬ እየተሽሎከለኩ ከሚወጡት ሴቶች ጋር እየተጋፋሁ ወደ መኝታ ቤቴ ገባሁና ልብሴን አወላልቄ ተኛሁ።

የምሳ ሰዓት ደረሰና ተዋበች ከመኝታ ክፍሌ ግድግዳ አጠገብ ሆና መልኳን ሳታሳየኝ «ምሳ እሱጋ ላምጣ እንዴ» አለችኝ፤ ጠራኋትና ከክፍሉ ስትገባ ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳታደርግና በቤቴም ሴትም ሆነች ወንድ ካለኔ ፈቃድ አንድም ሰው እንዳይገባ አስጠንቅቄ ነገርኳት። እሷም ሁለተኛ እንደምታደግመውና አሁንም በወር አንድ ጊዜ ብድር መክፈልዋን ነግራኝ ይቅርታ ጠየቀችኝ።

በእርግጥ ጥፋት ማጥፋታዋ ቢታወቅም ገረድ መለዋወጡ ሰልችቶኝ ነበርና ታገስኳት፤ በተለይም ያስመረረኝ አንዳንድ ሰዎች በማያገባቸው እየገቡ ምን አረመኔ ቢሆን ነው ገረድ የማያኖረው? ይሉኝ እንደ ነበረ ስለማውቅ በዚህ ሁሉ ይሉኝታ ትሁን እስቲ መንፈቅ እንኳ እያባበልኳት ትድፈን ብዬ ተውኳት።

አንድ ቦታ እገዛለሁ ብዬ ብድር ለመጠየቅ ከባንክ ብሔድ ለዋስትና የምታሲዘውን ካርታ አምጣ አለኝና አወደ አሥር ሰዓት ገደማ ላይ የቦታ ካርታዬን ልወስድ ከቤት ብሔድ አሁንም ደግሞ ከዚያ በፊት እንዳየሁት የሴት ብዛት አላስገባ አለኝ። የማላውቃቸውም ተጨምረዋል፤ ቤቱ በጢጅ የተወለወለ ይመስላል ያውዳል። አሁንም እንደተለመደው ሲሸባበሩ ተዋበች ምን ዕዳ ነው እቴ ስትል ተሰማኝ።

ከቁም ሣጥኑ ውስጥ ካርታዬን ይዤ ተመልሼ ሔድኩ፤ ስመለስ እንኳን እንደ በፊቱ አይብዙ እንጂ ከቤት ውስጥ የማላውቃቸው ሴቶች አልጠፉም ነበር፤ ገባኝ፤ ብዙ ነገር እንዳባከነብኝ ተገዘብሁ፤ በእርግጥ ደግ ሰው ናቸው ልባል ይብቃ አልኩ።

በየቀኑ የምሰጠው የቤት ወጪ ለጢጅ መግዣ መሆኑን አወቅሁ፤ ምግቤም ትርፍራፊ መሆኑ ተሰማኝ፤ የብዙ ሰዎች ስም ከቤቴ ውስጥ ሲወስድና ሲኮስስ እንደሚውል አወቅሁ።

እኔውም ብሆን እኔው ራሴ በራሴ ግብዣ ስታማ እንደምውል ገባኝ፤ በተለይም ለማየትም ሆነ ለማነጋገር የምንቃቸውና በሩቅ የምጠላቸው

የመንደር ምላሰኛ ሴቶች በቤቴ ውስጥ ባለቤት ሆነው በመገናኘታቸው ነደደኝ ቆጨኝ፤ አንገበገበኝ። ማታ ከቤቴ እያዘንሁ ስመለስ አንድም ሰው ሳላገኝ በቀጥታ ከመኝታ ክፍሌ ገባሁ፤ ጥቂት እንደ ቆየሁ ተዋበች መጥታ «ሻይ ላምጣ» አለችኝ፤ የሆዴን በሆዴ እሺ አልኳት።

ሻዩን ሰጥታኝ ልትመለስ ስትል «ዛሬ ጌቶች ተቆጡኝ መሰለኝ» አለችኝ፤ እኔም ያልተናደድሁ መስዬ «የለም አልተቆጣሁም፤ በደሞዝሽ ባደረግሽው ነገር ምን ያስቆጣናል» አልኳት፤ ተዋበች ደስ ብሏት ሔደች፤ ሽር ጉድ ብላ እራቴን አብልታኝ ተኛሁ፤ ጧት በማለዳ ተነስቼ ቁርሴን ከበላሁ በኋላ፤ «በይ ሳልሔድ ልብስሽን ይዘሽ ውጪ» አልኳት፤ ምነው? አለችኝ፤ ምንም አይደለምና ብቻ ውጪ ብያት አንድ ብርድልብስና አንሶላውና ከፊቴ አራግፌው ብዬ አራግፋው ሔደች፤ ጐረቤቶቼ እየገቡ የሚወጡትን የገረዶቼን ብዛት እየቆጠሩ እንደሚታዘቡኝ አውቃለሁ፤ ይሁን ስለኔ የማውቀው እኔ ነኝ።

# ምዕራፍ ፳

የገረድ ችግር እያስቸገረኝ ከረመ፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ብፈልግም ባስፈልግም ላገኝ አልቻልኩም፤ የምጠይቃቸው ሁሉ የቡና በጠራ ጊዜ ነው ይሉኛል። መገኘት አይቀርምና የቆየሁትን ያህል ቆይቼ አንዷን ደግሞ አገኘሁ፤ እንዳገኘሁም ሰዎቹ አንተ ገረድ አልበረከትልህ የሚልህ ሁሉ ሥልጣን እየሰጠኋቸው ነው አሉኝ።

እንደ በፊቱ ፋር ላለቃቸው በሆዴ ለሆዴ ማልሁ፤ አዲስቱን ገረድ አስናቀችን «እንግዲህ የቤቱ ጠቅላይ ገዥና አስተዳዳሪ እኔ ስለሆንኩ እንደፈለግሁ የማዝሽ እኔ ነኝ» አልኳት «እሱንማ አውቃለሁ፤ ብቻ በሥራዬ ላይ እንደ ልቤ መሆን አለብኝ» አለችኝ።

«እሱን ተይውና የምልሽን ስሚ» አልኳት «በመሥሪያ ቤቴ በሥራዬ ላይ አለቃ አለኝ፤ አለቃዬ ሁሉዋን ነገር ጨብጠው ይዘው እኔ እንዳልኩ ብቻ ሥራ ይሉኛል፤ እኔም ለማደሪያዬ ብዬ እንዳሉኝ እሠራለሁ፤ ተው ያሉኝን እተዋለሁ፤ ተቀመጥ ሲሉኝ እወዘፋለሁ እንጂ ካልሔድሁ ብዬ

አልጋተርም፤ አትለፍልፍ ሲሉኝ አልጮህም በመሰላቸው መንገድ ሥራ ሲሉኝ እንደሚመስላቸው አድርጌ እሠራለሁ፤ ዘባራቂ ነህ ሲሉ አለመሆኔን ባውቀውም አዎን ብዬ አምናለሁ፤ ለእንጀራ ስል ነው፤ ባፈነግጥ አስፈንግጠው ይጥሉኛል» ስላት «አይቆጡኝና አንዴ ልጠይቆት» አለችኝ።

«አለቃዎ ብሥራዎ ቢገቡ ሥራውን ያውቁት ይሆናል፤ የእርሶ በሥራዬ መግባት ሥራዬን አያበላሽምን» አለችኝ፤ «የፈቀደው ይሁን» አልኳት እኔ ደግሞ «በመሰላቸው እንደሚያሠሩኝ በመሠለኝ መሥራት አለብሽ ያለ ጌሾ ጠላ ጥመቂ ብልሽ መጥመቅ ነው፤ እኔ እንደማደርገው ሁሉ አንቺ ማየት ያለብሽ ደምወዝሽን ነው፤ እንደወላድ ቀንሽን መቁጠር ነው፤ ደሞዝ ቢጨመርልኝ ይጨመርልሻል፤ ቢቆረጥብኝ ይቆረጥብሻል፤ ቢቀጡኝ እቀጣለሁ፤ ቀጥሬሻለሁና ንዴቴን ሁሉ እወጣብሻለሁ» አልኳት።

«ታዲያ ካሁኑ ጀምረን የተጨቅጨቅን እንዴት እንዘልቀዋለን? » አለችኝ፤ «ሕግ ነው፤ ለደሞዝሽ ስትይ መቻል አለብሽ ላፈንግጥ ብትይ አስፈንግጬ እጥልሻለሁ፤ ጥፊም አለብሽ፤ ለዚህ ሁሉ እንዳንበቃ እኔ እንዳልኩሽ መኖር አለብሽ» አልኳት «ይሁን» አለችኝ እንደተከዘች «ንግግር አልወድምና እንዲሰድቡኝ ብቻ አልፈልግም ብትለኝ «ሕግ ነው» አልኳት።

ነጠላዋን አጣፍታ እንደ ቆመች አንገቷን አወላግዳ እያየችኝ «እንዴ? ተሳደቡ የሚል ሕግ አለ እንዴ? » አለችኝ፤ «የለም፤ ግን አለቆቼ በየአእምሮአቸው የደነገጉት በመሆናቸው እኔም አሜን ብዬ የተቀበልኩት ነውና አንቺም እኔን በቦርሳው እምጀን ብለሽ መቀበል አለብሽ» ብላት «ይሁን እስቲ እንሞክረው» ብላኝ አንገቷን አቅለሰለሰች፤ «ድሮም የምቀጥራቸው ከሙከራው ጊዜ አያልፉም ቢያባብሏችሁም ባያባብሏችሁም ያው ናችሁ፤ በይ አሁን ግቢና ሥራሽን ጀምሪ» አልኳት።

አስናቀች ሁለት ወር ደህና አድርጋ ሠራች በኔም ተቆጣጣሪነት ሥር ሆና ቁጣዬንም ግልምጫዬንም ችላ ኖረች፤ በእርግጥ ገረዶችን ተቆጣጥሮና ተቆጥቶ ማስተዳደሩ ጥሩ የአስተዳደር ችሎታ መሆን ተገንዘብኩት።

ላለፉት ገረዶቼ የዋህ መሆኔም ካለፈ በኋላ ቆጨኝ፤ አስናቀች ብልጥ ናት፤ በብልጠቷም የምላትን ነገር ሁሉ እንዳልኳት ትሠራለች፤ ከክንፈ ጋር ከበኢት የመጣን ዕለት የገረዴን የአስናቀችን አሰለጣጠን ለክንፈ ለማሳየት ያህል ጠላ የጠጣሁበትን ብርጭቆ አስናቀችን እርቼ እንቺ ስበሪው ብላት ወዲያውኑ ተቀብላኝ ከበረንዳው ላይ ሰባብራ ጥላ ተመልሳ እጅ ነሣታኝ «ድሮውንም ይህን ብርጭቆ አልወደም ነበር» ብላኝ ወደ ጓዳ ገባች ክንፈም ገረዴን እንዴ እንዳሰለጠንኳት ገርሞት እርሱም ከኛ በኢት አጥንቶ ገረዱን ሊያሰለጥን ሔደ።

አስናቀችን በቀጠርኳት በሦስተኛው ወር ላይ የሦስተኛ ወር ደሞዝን በከፈልኳት ማግስት «ያሰናብቱኝ» አለችኝ «ለምን» ብላት «በቃኝ» አለችኝ።

«ምን ተበደልሽና ትሔጃለሽ»

«አልተበደልኩም ብቻ በቃኝ»

«ምን ተነሻክና፤»

«አልተነካሁም ብቻ በቃኝ፤»

«ምክንያቱን ካልነገርሽኝ አትሔጅም፤»

«ምን ያደርግሎታል፤»

«መንገር አለብሽ»

«ሌላ ጋ በተሻለ ደሞዝ ሥራ አገኘሁ፤»

«ፈጽሞ መሔድ የለብሽም፤ አሰልጥኘ አሰልጥኘ አለቅሽም፤»

«ቦታው እንኳ እርሶ ላሰለጠኑኝ ሞያ የሚሆን አይደለም»

«የት ነው»

«መጠጥ ቤት ለመክፈት ነው፤ እስቲ ልሞክረው ብዬ ነው»

«እንግዲህ የናንተ ዕድገት መጠጥ ቤት መክፈት ነው? »

«ሌላ ምን እንሥራ? እሱው ነው ተስፋችን»

«አያዋጣሽምና ይቅርብሽ»

«ልሞክረው»

«ትከስሪያለሽ»

«ከከሰርኩም እንደ ገና ደግሜ እቀጠራለሁ»

«ስትመላለሺ ልትኖሪ»

«ምን ይደረግ»

«ተይ ቅሪ»

«እኔስ እሔዳለሁ»

«መሔድ የለም አርፈሽ ሥራሽን ሥሪ»

«እሔዳለሁ ብያለሁና መሔድ አለብኝ»

«ስትሔጂም ብያለሁና መሔድ የለብሽም»

«አልኩና ገላምጫት በቁጣ እየተራመድሁ ወደ ሥራዬ ሔድሁ በሰዓት ከቤቴ ብመጣ ቤቱን ጥላልኝ ሔዳ አገኘኋት።

ከሰዓት በኋላ ለመሥሪያ ቤቴ ተላላኪ ለበለጠ ገረድ እንዲፈልግልኝ ነግሬው በማግሥቱ ወለተ መድኅንን አመጣልኝ፤ ወለተ መድኅን ድሮ የፊታውራሪ አካሉ ስለ ነበረች ደህና ሞያ ያላት ናት፤ ነፃ ከመውጣትዋ በፊት እመቤትዋ ወይዘሮ ለወጓ እየገረፏት ደህና አድርገው እንዳስለጠኗ አጫውታኛለች።

ጌታዋን ፋሽስቶች ገድለውባታል፤ እመቤትዋን ደህይተው ጠላ መሸጥ ሲጀምሩ በአሻሮ ምች የተነሣ መሞታቸው ሁሉ አጫውታኛለች፤ ካቶ በላይነህ ቤት ተቀጥራ በስምንት ዓመትዋ መውጣቷንም ነግራኛለች። የወጣችበትም ምክንያት አቶ በላይነህ ደብሪቱን ስላገቡና ደብሪቱ ገና ልጅነቷን ያልጨረሰች በመሆንዋ መሆኑንም አውርታልኝለች፤ ብቻ

በጠቅላላው ጠቅላላው ምክንያት ወለተ መድኅን ካቶ በላይነህ ቤት የተባረረችው በሴት ነገር ነው።

ከቤቴ ከገባች በወርዋ አንድ ጠና ያለ ሰው አየሁባት፤ ምናልባት ዘመድዋ ይሆን ይሆናል፤ እያልኩ ተወት አደረኳት፤ ነገር እየበዛ ስለ ሔደ አንድ ቀን ከእልፍኝ ጠራኋትና «ይኸ ሰውዬ ምን ያመላልሰዋል፤ ምን ጉዳይ አለው» ብላት «ኧረ ባክዎቴ ያስቸግረኛል» አለችኝ።

«ምንድነው የሚያስቸግርሽ»

«ኧረ ባክዎት እኔ እየፈራሆት ነው እንጂ እሱስ የሚለው ሌላ ነው»

«ምንድነው የሚለው»

«ኧረ ባክዎትን ጉድነው ምን ዘመን ላይ ደረስኩ»

«ምንድነው እሱ»

«ኧረ ባኮት አይ ስምንተኛው ሺ»

«ምንድነው የሚልሽ?

«አይ ጊዜ - ምነው ሞቼ ባረፍኩት»

«ተናገሪ እንጂ»

«ምን እባክዎ የቀፈፈ ነገር ነው»

«ምንድነው»

«እሱ የወይዘሮ በላይነሽ አሽከር ነው»

«የቷ በላይነሻ»

«እኒያ ባላቸው በመኪና የሞቱባቸው»

«ታዲያስ»

«ታዲያ እንዲያው ዝም ብሎ ይመላለሳል ይመላለሳል - ስንቴ መሰሎት ያስቸገረኝ»

«ላግባሽ ነው የሚልሽ»

«እሱማ ቢሆን ወግ - ድሮም ወንድ ሴትን መለመኑ እውቅ ነው»

«ታዲያ»

«ምን ባኮት ንገሪኝ ይለኛል»

«ለማን»

«ለእርሶ»

«ምን»

«ስለ ወይዘሮ በላይነሽ ነዋ»

«ምን ሆኑ»

«ምን ይሆናሉ - ኧረ ባኮት ያሳፍራል»

«ምንድነው»

«እንግዲህ ወይዘሮ በላይነሽ ወደርሶ ይልኩታል - አገናኚኝ ከጌቶች ጋር ይለኛል - ታዲያ ፈራሁ»

«ምን ያስፈራሻል? ምን ያገባሽና ነው የምትከለክይው? »

«እሱስ ነው - ብቻ ነገሩ አያምርም»

«ሰምተሸዋል እንዴ? »

«ኋላ ጉዱ የት ሆነሎት - ባልስማማ ምንቸገረኝ»

«ምንድነው»

«ላግባቸው ይላሉ»

«ማ»

«በላይነሽ»

«ማንን»

«እርሶን»

«ታዲያ ምን ያስፈራል» ብላት «እንግዲያው ነገ ሲመጣ አገናኞታለሁ» አለችው ወደ ጓዳ ወደ ሥራዋ ሔደች በላይነሽ ደስ የምትል ቆንጆዬ ልጅ መሆንዋን አውቃለሁ ላገባትም እየከጀልሁ ባሏ ሞቶባታልና ምናልባት እሺ አትለኝም በማለት ቆይቻለሁ፤ ደፍራ ላግባህ ብላ በመላከዋም ደስታም ኩራም ተሰማኝ።

አሽከርዋን ገብሬንም አነጋግሬ ላገባት ደስተኛ መሆኔን ነግሬዋለሁ፤ ገብሬም ሁል ጊዜ እየተምላለሰ መልእክቷን ነግሮኝ መልእክቴን ይዞላት ይሄድ ጀመር፤ ከምሰጠ ጉርሻ ሌላ ከኔም ቤት ቤተኛ ሆነ፤ ከበላይነሽ ጋር አገናኝቶኝ ቃል በቃል እንድንነጋገር እንዲያደርግ ብጠይቀው «የባላቸው መንፈቅ ስለ ደረሰ የባልዮው ዘመዶች ከቤት ስላሉ ይህን ነገር በጥርጣሬ አውቀዋልና ይጣሉኛል እያሉ እሜቴ ስለ ሰጉ ነው እንጂ እሳቸውም ለመነጋገሩ ይፈልጉ ነበር» አለኝ።

«እንግዲያውስ ለምን ከኔ ቤት አትመጣም» ብለው «ከቤት አይወጡም ቢወጡም ከባላቸው ዘመዶች ጋር ስለሆነ ነገሩ አስቸግሮ ነው፤ አይ ጌቶች - እኔስ ብሆን ይህን ሁሉ የማላስብ ይመስሎታል» አለኝ።

ታሪኩን አላራዝመው፤ ባጭሩ ይቀጭ፤ ባጭሩ እኔና በላይነሽ ተጋባን፤ ወደድኳት እሷም ብትሆን ወዳኝና መርጣኝ ደግሞም ሳትታጭ አጭታኝ ያገባችኝ በመሆንዋ እንደምትወደኝ ይገባኛል፤ አዘውትራም ስለምትላፋኝና እንድቃለዳት ስለምትፈልግ በእርግጥ እንደምትወደኝ አውቃለሁ፤ አንዳንዴም ታጭቼ የተገባሁ በመሆኔ ለመኩራትም ይቃጣኛል፤ ያም ቢሆን እወዳታለሁና ፍቅር ኩራቴን ያሸንፈዋል።

በጊዜ ገብቼ ካልጋዬ ላይ ጋደም ብያለሁ፤ በላይነሽ ከወገቤ አጠገብ ካልጋው ላይ ተቀምጣለች፤ የቀልድ ጭውውቶች ተጫውተን፤ «ለመሆኑ» አልኳት «ምንምኔ ቢጥልሽ ነው ላግባህ ብለሽ የላከሽብኝ» ብላት «እኔ ልጅት፤ አንተ ነህ እንጂ የመግባቢያና የመውጫ ጊዜ አሳጥተኸኝ ካላገባሁሽ ብለህ ያገባኸኝ፤ ደሞ ምንህ ይለመናል፤ ደሞስ እኔ ነኝ ላግባህ ብዬ

የምለምንህ» ብላ ዓይንዋን እንዳፈጠጠችብኝ አገጭዋን በእጅዋ አስመርኩዛ ታየኝ ጀመር።

እንደመደንገጥም ብዬ ግንባሬን ኮስተር አደረኩና «ወይጅ ባክሽ ወሬ ለውጭ» ብላት «መች የሚለወጠውን ጀመርክና - ለመሆኑ እስከ ዛሬ ተለምኜ የተገባሁ ነኝ ትል ነበር እንዴ» አለችኝ።

«አዎ» አልኳት

«እንዴት ብለህ? » አለችኝ

«ላግባህ ብላ ለምናኝ አገባችኝ እያልኩ ነዋ» አልኳት

«ምነው አንተው አይደለህ እንዴ አበድኩ፤ - ሞትኩ ካላገኘሁሽ ነፍሴ ይወድቃል በልህ ፎክረህ ጎዘኔን ሳልጨርስ ያገባኸኝ! አይ ወድኖች ደሞ ተለምኜ ነው ይባልልኛል» አለችኝ።

«ምስክር አለኮ» ብላት

«ይኑራ እስቲ ይመስክር - ማነው እንዲያው በላይነሽ ለምናው አገባችው የሚል? ሰይጣንም አይመሰክር፤ እርግጥ አንተ ማስቸገርህን ይመሰክሩብሃል» አለችኝ፤ እንግዲያውስ ገብሬ ይጠራ አልኩና ግብሬ ተጠርቶ መጣ፤ ከውገቤ ቀና ብዬ ቁጭ አልኩና በላይነሽ በእጅዋ አገጭዋን እንደተመረኮዘች አፍጣ ገብሬን ስታየው «ያኔ ምንድነው ያልከኝ? » ብዬ ብጠይቀው ገብሬ አተኩሮ እያየኝ «መቼ» ብሎ ጠየቀኝ።

«እኔና በላይነሽ ሳንጋባ በፊት» ብለው

«ምን አልኩ» አለኝ።

«እሜቴ እርሶን ካላገባሁ እያሉ አስቸግረውኛል እያልክ አልነገርከኝም? » ስለው በላይነሽ ከተለመደው በርከት አድርጋ ተንፍሳ የተመረኮዘችውን እጅዋን ለቃ ሁለቱንም እጅዎችዋን ወደ ኋላዋ ዘርግታ አልጋውን ተመርኩዛ ለጠጥ ብላ ተቀመጠችና ገብሬን አተኩራ ትመለከተው ጀመር።

ገብሬም ወደ ኋላው አፈገፍጐ ግድግዳውን ተደግፎ ቆመና «አዎ ብያለሁ» አለ፤ በላይነሽ ተቆጥታ ቀና ብላ ቁጭ አለችና «እኔ? » ብትለው «አይ እርሶ አይደሉም» አለ፤ «እንዴ ያኔ እሜቴ ካልገብሁት ብለዋል እያልከኝ ታስቸግረኝ አልነበረም» ብለው «አዎ» አለኝ።

በላይነሽ በጐን አስተያየት እያየችው «ኧረ እንዲያው ምንጊዜ ነው እንዲህ ብዬ የላኩህ? » አንተ ቀጣሪ» ብትለው «ብለውኝም አያውቁ» አላት፤ «እንግዲህ አትቃዥ» አልኩት፤ «ትናገር እንደሆነ እውነቷን ተናገር፤ እኔ ስጠይቅህ አዎ እሷ ስጠይቅህ አዎ ማለቱ አያዋጣም» ብለው እራሱን አካከከና «እስቲ ለሁሉም ነገር ወለተ መድኅንን ትጠየቅ» አለ «በል ጥራት» አልኩት ሊጠራት ሄዶ አምስት ደቂቃ ያህል ቆይቶ አብረው መጡ።

«በይ ወለቱ ያኔ ገብሬ ምን ነበር የሚለኝ? » ብላት

«ምን አለ» አለችኝ

«እመቤቴ ጌታሽን ካላገባሁ ብለው አስቸግረኛል አላልሽም» ብላት «ማለቱንማ ብሎኛል» አለችኝ ገብሬ ወደ ወለቱ እያየ «እኔ ነኝ በፊት ያልኩሽ» ቢላት ወለቱ ገብሬን ገርምማው አንገቷን ጠምዛ በጐን እያየችው «አሁን አትዝረጥረጥ ምንድነው ሽሙጥሙት ሽሙጥሙጥ ማለት፤ ነውር ነው፤ አላጠፋን፤ አልሰረቅን፤ የምን መርበድበድ ነው» አለችውና ፊትዋን ወደኛ አዞራ «ውሸት መናገር ኃጢአት ነው» አለችውና አባ ተክለየስም ይህን ሁሉ ሲናገሩ ጆሮዬ ሰምቷል፤ ያጋባናችሁ በውሸት ነው» አለች።

«እንዴት ነው ውሸቱ? » ብላት «እርሶም አልተናገሩም፤ እሜቴም አልተናገሩም፤ ሁሉን ያወራነው እኔና ገብሬ ነን» አለች በላይነሽ አሁንም ካቅሟ በላይ ተነፈሰችና እግርዋን አደራርባ ተቀምጣ «ለመሆኑ እንዴት ወጠናችሁት» ስትል እኔ አቋረጥኳትና በጀርባዬ ተንጋልዬ «ሥራው ጥሩ ነው፤ የኃጢአተ አይደለም፤ ለመሆኑ እንዴት እንዳሰባችሁ እስቲ ንገሪን» አልኳት።

ወለቱ ሁለቱንም እጆችዋን እያሠራች «ገብሬ እኔን አስቸግሮ ያዘኝ» ስትል በላይነሽ አቋረጠቻትና «ምን ብሎ ነው ያስቸገረሽ» አለቻት «ቆይ አታቋርጫት» ብል «እየተጣራ እንስማው እንጂ» አለች በላይነሽ።

«ገብሬ ያስቸገረኝማ» ስትል ወለቱ ወሬዋን ጀመረች «ልወዳጅሽ እያለኝ ነው፤ የማይሳሳት የለምና ተሳስቼ ከገብሬ ጋር ተወዳጀን፤ ተዋደድን፤ ብዙ ጊዜ አዳሩ ከኔ ጋር ሆነ፤ አንዳንዴም ጌቶች ያዩት ጀመር በኋላ እስተምልከቱ ጌቶች ያቺን ቀይ መጣፍ ሲያነቡ ይሄ ሰውዬ ለምን ይመጣል አሉና ጠየቁኝ ደነገጥሁ የምሰጣቸው መልስ አጣሁ፤ ጌቶች ቢያጣድፉኝ ለጊዜው ለመውጫዬ ብዬ እመቤቱ እርሶን ላግባ እያሉ እየላኩት ነው ብዬ ተነፈስሁ፤ ደንግጬ ነው እንጂ ገብሬም አልነገረኝም።»

«በኋላ ለገብሬ ነገርኩት» ስትል አሁንም በላይነሽ አቋረጠቻትና «ምን ብለሽ» አለቻት፤ «ገብሬ? ጌቶች እንዲህ ብለው ቢጠይቁኝ እንዲህ አልኳቸው ምን ይሻላል ብለው እኔ ምን አውቃለሁ አለኝ፤ እንግዲያውስ እኔም አንተም እንድንኖር በነገሩ እንግፋበት ብለው እንዴት አርገን አለኝ አንተ ለእመቤትህ ሰውዬው አስቸገረው ይልኩኛል እያልክ እያሳመርክ ንገር፤ እኛጋ ስትመጣ ደግሞ እሜቴ እንዲህ ብለዋል እያልክ ንገር አልኩት፤ ውሸት ምን ያደርጋል በዚህ መሐል እኛ ሳንለያይ ፍቅራችንን እንጨርሳለን ብለን ነበር እንጂ ያሰብነው እውነት ትጋባላችሁ አላልንም ነበር፤ የእግዜር ነገር ታምር ነው ተጋባችሁ» አለች፡

እኔ ጥያቄና ነገር ላበዛ ነበር፤ በላይነሽ ግን «ግሩም ነው» አለችና በይ በቃችሁ ሒዱ አለቻቸውና ገብሬም ወልተመድኅንም ወደ ማድቤታቸው ሄዱ፤ እኔና በላይነሽም የጠብ ሳይሆን በነገር ማውጠንጠን ተኳርፈን ራት በላንና ተኛን።

በላይነሽ ልትተኛ ልብስዋን ስታወላልቅ «እነኝህ በሀሰት ሰውንም ያጋድላሉ» አለችና «ቆይ እኔ አይደለሁም» ብላ ዝታ ተኛች፤ በማግሥቱም ከሥራ ስመለስ ገብሬንም ወለቱንም ማባረርዋን ነገረችኝ።

# ምዕራፍ ፮

ከበላይነሽ ጋር ሆነን ሦስት ገረዶች አሰናበትን፤ የበላይነሽም ሆነ የኔ ዓመል ለገረዶች የማይስማማ ሆነ፤ የገረዶቹም ዓመል ለኔም ሆነ ለበላይነሽ አልስማማችሁ አለን።

ከበቡሽ ለሦስት ወራት ያህል ጥሩና መካከለኛ ገረድ ሆና ኖረች፤ ሦስተኛው ወር እንዳለቀ መለገም ጀመረች፤ ሲጠሯት የሚስማውን ጆሮዋን እንደማይሰማ አደረገችው፤ ከእልፍኝ እስከ ማድቤት ያለው መንገድ ራቃት፤ መመላለሱም ሰለቻት፤ ስትታዘዝም ማጉረምረም ጀመረች።

አንድ ቀን በላይነሽ ስትጠራት ከጠሪና ከተጠሪዋ አማሃይ ቦታ ያለሁት ስሰማ «እንግዲህ ጀመረች ይቺ ቆፍቋፋ አሮጊት ውጋት ይመስል ቀስፋ ትይዛለች ይቅሰፍሽ» አለችና «እመት» አለቻት፤ የበላይነሽን ልጅነት አውቅ ነበርና ስድቡ ፍሬ የሌለው ነው።

እንለፈው ብዬ እንዳልሰማሁ ሆኜ ዝም አልኩ፤ አንድ ቀን ድግሞ እኔ ካንዱ ክፍል ሆኜ በላይነሽ ከበቡሽን ያዘዘቻትን አላውቅም በመተላለፊያዋ ስታልፍ «የምን መጨማለቅ ነው፤ እፉኝት፤ ከርሳም የሰው ከርሳም እያለች እያጉረመረመች ስታልፍ ሰማኋት።

አሁንስ ነደደኝ ግልፍ አለኝና ከበቡሽን ጠራኋትና በሦስተኛው ጥሪዬ ሰምታኝ መጣች፤ «ለምን ትሳደቢያለሽ ብላት «መቼ ተሳደብሁ» አለችኝ፤ «አሁን ስትሳደቢ አልሰማሁሽም» ብላት «አይ እኔ አናቴ ለራሴ በበሽተኛ ጉኔ ጭቅጭቅ አልችልም» አልችና ልትሄድ ስትል ከወደኋላዋ የማጅራቷን ቀሚስ ይዤ ስቤ መለስኳትና ፊትዋን ስታዞር አንዴ በጥፌ አልኳት።

በጩኸት መንደራችንን እያሸበረች ሄደች፤ በላይነሽ መጥታ «ምነው ምንሆናችሁ» ብትለኝ «ስትሰድብሽ ሰምቼ መታኋት» አልኳትና ጥቂት ቆይቼ ወደ ሥራዬ ሄድሁ በሰዓት ወደ ቤቴ ስመለስ ከበቡሽ ከመንገድ ላይ ጠብቃኝ የፖሊስ ጣቢያ መጥሪያ በእጅዋ ይዛ እንኩ በማለት ፈንታ እንካ አለችኝ «ወይጅ ጨምላቃ የምን መጨማለቅ ነው» ብያት ሳልፍ «ልብ

አርጉልኝ እንደ ገና ደግሞ ሊሰድበኝ፤ የግራውም የቀኙም ልባርጉልኝ ብቻ፤ በሕግ በተቀባው ንጉሥ እንካ ተቀበለኝ» አለችኝ።

አንድ ሳያብድ ያበደ የሚመስል ሽበት የወረረው ቢጤ «ምንድነው አንቺ ወልዶ አላሳድግ አለ እንዴ አላትና ወደኔ እየተመለከተ «ድሮውኑ አለመጠጋት ነበር እንጂ ያንተን ዲቃላ እሷ በምንዋ ታሳድገው፤ ክፈል» አለና አለፈ።

ከበቡሽ ምን ይሄ ደሞ ይዘባርቃል ስትል የሰማት ጉጭባ ጐረምሳ «አልከፍል አለ? ከኪሱ ሳይኖረው ለምን ጠጣ? ባብዬ ደህ» አለ፤ ለጐረምሳው መልስ ለመስጠት ስሰናዳ አንዱ ጫማ ጠራጊ ደግሞ «አንቺ ሱፍ የለበሰ ሁሉ ጌታ መስሎሽ ነው በዱቤ የሰጠሽው? ኧረ ያንተን እልም ያርገው» አለችው፤ ያው ጫማ ጠራጊ መለሰና «ዓይንሽ ይጥፋና ደግሞ ትሳደቢያለሽ? » ብሎ ሲጠጋት «በሕግ አትጠጋኝ» አለችው።

በነሱ ግርግር መሐል መንገዴን ልጀምር ስል «በሕግ አምላክ አንተ ሰውዬ እንካ ተቀበለኝ አንተ ሰውዬ እንካ ተቀበለኝ አለችኝ፤ ከቦ የሚያየንና የሚያዳምጠን ወሬኛ ሁሉ «ባንድ ቃል» አይቀበላትም እንዴ? ሱፍ የለበሰ እንደሆን ምን መስሎታል» እያሉ አውካኩብኝ።

ለመሔድም ሆነ በሰላም ቆሞ ለመነጋገር ስላልቻልኩ በቀሪው ላይ ፈርሜ መጥሪያውን ተቀበልኳት ወዲያውኑ ያ ሁሉ አጀብ ሄ - ሆ ይሮ እያለ አወካ፤ ሌባ ይመስል በመሐላቸው ሾልኬ አለፍኩ፤ አጀቡ ከከበቡሽ ጋር እያውካካ ሔደ።

መጥሪያው በጠራኝ መሠረት በዘጠኝ ሰዓት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ሄድሁ፤ ቃሌን ሊቀበለኝ የተሰናዳው ፖሊስ «ትልቅ ሰው ሆነው እንዲህ ይሠራሉ ወይ? » አለኝ? «ምን ሠራሁ? » አልኩት «ነውር ነው፤ ድሆች ወዴት ይግቡ ነው የምትሉት? » ሲል ግድግዳውን ተደግፋ እጆችዋን ወደ ኋላዋ ግርግዳው ላይ ለጥፋ የቆመችው ከበቡሽ «መግቢያ አጣን፤ ማንም እየተንሳ ይደበድበን ጀመር፤ ምንስ» ብላ ልትቀጥል ስትል እወረቀቱ ላይ ብዕሩን አሳርፎ ጽሑፉን ያሳምር የነበረው ፖሊስ ቀና ብሎ እያያት «ዝም

በይ! መላሰኛ! ይሄው መላሳችሁ ነው ሰውን ወንጀል የሚያሠራው» አላትና አቀርቅሮ መጻፉን ጀመረ።

የወንጀለኛ አጠያየቅ ስነ ሥርዓታቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት እንደመሰለው ጠይቆኝ እንደሚመስለኝ መለስኩለት።

«መተዋታል? »

«አዎ»

«ለምን»

«ስላናደደችኝ»

«እንዴት አናደደችዎት? »

«ሚስቴን በመስደብዋ»

«ከሳሽዋ ሲመቱኝ ማንም አልነበረ ብላለች፤ ታዲያ» ብሎ ሳይጨርስ ከበቡሽ ጣልቃ ገባችና «አዎ ጌታዬ እመኝታ ቤታቸው በር ላይ ነው የመቱኝ» አለች፤ ለፖሊሱ ሳቅ አለና «የመኝታ ቤቱን ነገር አቆይው» ብሎ አቀርቅሮ መጻፉን ጀመረና «እንግዲህ ዝም በይ እንሥራበት» አላት።

«እሺ ጌታዬ ይቀጥሉ» አለኝ

«ምን ልቀጥል» አልኩት

«ለምን መቷት»

«አናዳኝ»

«በምን ምክንያት አናደደችዎት? »

«ሚስቴን ሰድባብኝ ብያለሁ»

«ታዲያ ብትሳደብ ትከሰሳለች እንጂ ትመታለች? »

«አዎ»

«ሕግ አይፈቅድማ»

«ሕግ በኋላ ነው፤ ነደደኝ መታኋት»

«ቢናደዱም መታገስ ነበረቦት»

«መታገስ አቃተኝ መታኋት»

«እሺ እሱ ይሁን፤ አሁን በደረሰባት ጉዳት ሊያሳክሟት ይፈቅዳሉ? »

«ምን ሆነችና»

«የተመትችው»

«አንድ ጥፊ»

«አዎ ጉዳት ደርሶብኛል ትላለች» ብሎ ፖሊሱ ቀና አለና በብዕሩ ከንፈሩን እየደበደበ ተክዞ ቢያይት ከበቡሽ «አዎ አለሜ ጆሮዬ አልሰማ ብሎኛል - እው እያለ ይጮህብኛል» ብላ የግራ ጆሮዋን እየሳበች አሳየች።

ፖሊሱ እንደ ገና ሊጽፍ አቀረቀረና «እው ካለ መስማቱ ነው፤ ወይጅ ባክሽ» አላት ለጥቂት ጊዜ ተክዞ ቆይቶ «እስቲ ውጪ» አላትና ከበቡሽ ስትወጣ ፖሊሱ ለብቻዬ «ምን ያረግሎታል ከዚች ጋር አፍ መካፈት? ለሱ ክብርዎ ነው፤ ደሞ ልጅቱ ምላሰኛ ቢጤ ነች፤ እንዲህ ዓይነት ሰው ስም ያጠፉል፤ ያልሆነውን ሁሉ አስመስሎ ያወራል ደሞ ያመለከተችው አለ፤ ከባድ ነገር ነው» አለኝ።

«ምንድነው» ብለው «እቤታቸው ብዙ ሰዎች እየተሰበሰቡ የሚሠሩት ሥራ አለ እኔም የተመታሁት እግርግዳ ሥር ተደብቄ የሚማከሩትንና የሚማማሉበትን ሳዳምጥ በድንገት ደርሰውብኝ ነው ብላለች፤ ሴትዮዋ ባመለከተችው እኔ ሀገሬንና መንግሥቴን የምወድ ስለሆኑንኩ የሚል ቃል ይገኝበታል ለእቂም መበቀያ ብላ እንዳመለከተችው ይገባኛል ቢሆንም አለ።

እኔም ጠረጴዛውን በክርኔ ተመርኩዤ በመዳሬ አገጬን ደግፌ «ሐሰትዋን ነው፤ ሀሰት መሆንም ልታውቁት ትችላላችሁ» ስለው ፖሊሱ

አቋረጠኝና «ይቆዩ ይስሙኝ፤ ሐሰት መሆኑ እውነት እስኪጣራ እርሶ መጉላላትዎ አይቀርም፤ እርግጥ ሀሰት ይሆን ይሆናል፤ ብዙ ሰዎች ከሰው ጋር ሲጣሉ የሚጎዳበትን መንገድ ይፈልጋሉ፤ ይህን እናውቃለን፤ ቢሆንም ገና ለገና ይህ ይደረጋል ብለን ያገኘነውንም ፍንጭ ዝም አንለውም» አለ።

«በዚህ በኩል ተጠርጣሪ ሆኜ እርምጃ ሊወስድብኝ የሚገባ ሆኜ ከተገኘሁ ደስ በሚያሰኛችሁ መንገድ ደስ የሚያሰኛችሁን ልታደርጉ ትችላላችሁ» ብለው ፖሊሱ ባርኔጣውን እያስተካከለ «ይሄ አይባልም፤ ላልሆነ ነገር በምን ምክንያት ይጉላላሉ» አለኝ።

«እንግዲያውስ እንዴት ላርግ? » ብለው «ጥቂት ገንዘብ ይስጧት ይታረቁ» አለኝ፤ እየነደደኝ በእርቁ መንገድ ተስማማሁ፤ ከበቡሽ ተጠርታ ገባች፤ እዚያችው ቦታ ከመዝጊያዋ ጥቂት ከፍ ባል ግድግዳዋን ተደግፋ ቆመች።

ፖሊሱ አካሉን ወደ እሷ አቅጣጫ መልሶ እግሩን አነባብሮ ተቀመጠና «አንቺ ባለጌ ነሽ፤ ነገሩን ሁሉ መርምረን እንዳገኘነው ውሽታም ነሽ» ሲላት ከበቡሽ አቋረጠችውና «ንዴ መመታቴ ነው? ሳልመታ ተመታሁ እላለሁ እንዴ» ብትል ፖሊሱ «ዝም በይ! አተልፍልፊ፤ ይቺን ምላሽን ይዘሻት ብትኖሪ ይሻላል» ሲላት አሁንም ከበቡሽ አቋረጠችውና «ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ የድሀ ዕንባ ጠባቂ ለሆነው የበላይ አቤት እላለሁ፤ መቼስ ምን አረጋለሁ» ብላ መዝጊያውን ልትከፍት ስትል «አንቺ ሴትዮ ዛሬ ጤናም አልያዘሽ? አርፈሽ ቁሚ» አላት ፖሊሱ - ከበቡሽ መዝጊያውን ለቃ መለስ አለችና «እንዴ ታዲያ እርሶ ለእሳቸው ሲያግዙ ምን ላርግ» አለች፤ ፖሊሱ ልማድ ሆኖበታል መሰለኝ ማጅራቱን አከከና ባርኔጣውን እያስተካከለ «አሁን አንቺም ዕዳ እንዳትገቢ ይቅርብሽ» አላት።

ከበቡሽ ግንባርዋን ኮስትራ አይንዋን አጮለለጮለችና «ምኑ» አለች፤ ፖሊሱ በቁጣ «ነገሩ ነዋ» አላት፤ «ለምን ብዬ? በምን ምክንያት» አለችው፤ «ዕዳ ትገቢያለሽ አላት ፖሊሱ - «የምን ዕዳ» አለችው ከበቡሽ።

«ሰው በሀሰት ከሰሸ በነፃ አትለቀቂም በዘዙ ረጅም ነው፤ እኔ መከሬሻለሁ ነገሩ እንዳየሁት አያዋጣሽም ቢላት «አይይ ለምን አያዋጣኝም ያዋጣኛል» ብትለው ፖሊሱ ኮስተርተር አለና «አትታረቂም? » አላት።

«እሺ በምን ዓይነት ነው ዕርቁ» አለች ከበቡሽ።

«ለተበደልሽው ሁሉ ትካሻለሽ« አላት ፖሊሱ

«እሺ እንዴት ነው» አለሽ ከበቡሽ

«እስቲ አንዴ ውጪ ቆዪ» አላት ፖሊሱ

ከበቡሽ ከክፍሉ ስትወጣ ፖሊሱ ወደኔ ዞር አለና «ጥቂት ገንዘብ ይስጧት ወዲያ መገላገል ነው» አለኝ፤ «ስንት ልስጣት» ብለው «ሠላሳ ብር የብቃታል፤ እንቢ ብትል እቆጣታለሁ በዚህ ከተገላገሉ የዱላዋ ካሣ መሆኑ ነው፤ የሌላው ወንጀል መቅረቱም አንድ ግልግል ነው፤ የዛሬ እንገር አንዴ ከተንጠለጠለ አይበጠስም፤ ወዲያ መገላገል ነው» አለኝ።

ፖሊሱ ስላደረገው የሽምግልና ተግባር አመስገንኩትና በኪሴ ከነበረች አርባ ብር ሠላሳውን ሰጥቼ አሥርዋን ከተትሁ፤ ወዲያውኑ «እርሶ ይሂዱ እኔ ነገሩን እጨርሰዋለሁ» ስላለኝ ከጣቢያው ወጣሁ።

በማግሥቱ ከበቡሽ ዘንቢ ይዛ ካንድ ጠረንገሎ ቢጤ አሽከር ጋር ስትሄድ አየኋት ወደኔም ጠጋ ባላ «በአሥር ብቻ ሆነ የኛ ግልግል» ብላኝ እየሳቀች እየተውረገረገች አለፈችኝ፤ «ለጤና ይበልላችሁ» ብያት ከሴይቼንቶ ተሣፈርኩ።

# ምዕራፍ ፯

ሚስቴ በላይነሽ ስለ አዲሲቱ ገረዳችን ስለ አሰለፈች በየማታው ብዙ ነገር ታወራልኝ ጀመር፤

«እንዲህ አትምሰልህ ቆንጆ ናት፤ ልስብ አጠባ የጀመረች እንደሆነ አፈርድቤ ታስግጠዋለች፤

እማድ ቤት የገባች እንደሆነ በትንሽ ነገር ብዙ ትሠራለች፤ አሁን የቀኑ ምሳችን አንድ ብር ሰጥቻት ነው ያን ሁሉ ዓይነት የሠራችው፤ ባለ ሞያ ነች፤ እንዲህ አትምሰልህ፤ ጠላም ጠንስሳለች አታየውም የቤቱንስ ዕቃ አቀማመጥ» አለችኝ።

«ተይ የፊት አመስጋኝ ለኋላ አሜታ ያስቸግራል፤ ገረዶች ሁሉ በፊት ባለ ሞያ መስለው ለመታየት ሲገቡ ደህና አድርገው ይሠራሉ፤ በኋላ ግን መጐተት ያመጣሉ፤ ይሰለቻሉ፤ ማስጋናሽን ሳተበዢ በኋላ የምታመጣውን ልግም አስቢ» አልኳት።

በላይነሽ ግራ ክንዷን ካንገቴ ሥር ወሰደችና በጀርባዋ ተንጋላ «እሷ ልጅዬ እንደነኛ ጋጠ ወጤዎች ዓይነት አይደለችም፤ በፊትም ከነበረችበት ቤት እንዲሁ ነበረች፤ አሉ፤ ታዲያ ምን ያደርጋል፤ በችጋር ስለቆሏት አልፈግልም ብላ ወጣች፤ ስምንት ዓመት አብራቸው ኖራለች አሉ» አለችኝ።

«ስምንት ዓመት መኖርዋን ማን ነገረሽ» ብላት

«እሷው አጫወተችኝ አለችኝ በላይነሽ፤

«እሷው ተመስጋኝ እሷው መስካሪ? » ብላት፤

«ለምን ብላ ትዋሻለች» አለችኝ በላይነሽ

«ለመኖር ብላ»

«አይ እባክህቴ» ተከናንባ ፊትዋን ዞራ ተኛች

እውነትም አሰለፈች መሰንበቻዋን ሁሉ በመልካም ትሠራ ጀመር፤ የሞያዋአን ልክና ምን ያህልም ተወዳጅነት እንዳላት ስትነግረን ከረመች፤ «መለገም አላውቅም፤ ለማን ብዬ እለግማለሁ፤ ምስጥ ለሚበላው ጉልበት? በስማም እቴ።

«በስመ ገረድ ገረዶች ሁሉ ስማችንን ያጠፉታል፤ አያርፉም፤ ክስክሶች ናቸው፤ መቆነጣጠር ይወዳሉ፤ እናውቃለን፤ ይሉና ሥር ሲሏቸው ማጣፊያው ያጥራቸዋል።

«የእፍፍ ኰሌጅ ልጆች ሁሉ ቡና በጠራው ሲቆም በየሰው ቤት ይቀጠሩና እየተጉደፈደፉ የገረድ ስም ያጠፋሉ። እነሱ ምን ቸገራቸው ቡና ብጠራ ሲጀመር ተመልሰው ይሔዳሉ።

«ለቤቱ አያስቡ፤ ለስማቸው አይቸገሩ፤ ወድምድም ያረኳትና ሾለክ ይላሉ፤ ደሞ አያርፉ ከጐረቤት አንድ ኩሊ ቢጤ ይወሽሙና ለሱው ማጕብደድ ይወዳሉ፤ አፈር ድቤ ይበላ! እግዜርም አይወደው፤ ምን ያረጋል በንጹሕ ሲሠሩት ነው እግዜርም የሚባርከው።

«እሜትዬ ይሙቱ አልሎትም እኔ ልሙትሎት ስንቶቹ መሰሎት የሰው ቆሽት የሚያበግኑ? እንደሚያዩኝ ነው፤ አልወድም ምናባቱንስና መጥቶስ ምን ሊደግፍ?

«በንጹሕ ሠርቶ አስደስቶ ደሞዜን ጨምሩልኝ ማለት ያኮራል፤ እግዚአብሔርም ይወደዋል፤ አንድ የኛ ጐረቤት ሰውዬ ገረድ ነበረች፤ የበጉን የኋላ እግር ወርቹን አውጥታ ለውሻ ስትሰጠው አይቼ ምነው እሳቸውን ባትፈሪ እግዜርን አትፈሪም? ምናልባት እኮ እሳቸው ባያዩሽ እግዜር ያይሻል ብላት ምናገባሽ ታዲያ እኔ ከዚህ ከገነቸረ ሥጋ ጋር ልገናቸርልሽ ነው አለችኝ።

«ጡር ነው፤ ደግ አይደለም፤ እጅ ይጥላል፤ ወንድ ልጅ ለራሱ ምን ያውቃል ከብት ነው። እንስሳ ነው፤ አፈር ይብላኝ? ታዲያ አይቀር፤ እግዜር ያይ ያይና ይጥላል፤ ይኸ ሁሉ ገረድ ስንኩልኩል በሽተኛ የሚሆነው ለምን መሰሎት? በዚሁ ነው፤ እየተልከፈከፉ ነው፤ አበስኩ ገብርኩ እቴ» ባል ጣትዋን ነከሰች።

ይህ አንድ ዕለት ማታ አሰለፈች ያወራችልን ነው፤ ይህን በመሳሰለው ቃልዋ አሰለፈች በቤታችን ታማኝና ተወዳጅ ሆኖ ለስድስት ወር ቆየች፤ አሰለፈች ምንም ታማኝ ብትሆን ሚስቴ በላይነሽም ጥንቁቅ ነበረችና ማድቤቱ ከተቆለፈ በኋላ የማድቤቱን ቁልፍ የማታሳድረው ከእስዋ ዘንድ ነበር፤ አንዳንዴ» አሰለፈች ማድቤቱን ቆልፋ ትመለስና መፍቻውን ከጠረጴዛው ላይ ወርወር ስታደርገው በላይነሽ ከመተኛትዋ በፊት የማድቤቱን መፍቻ ስጪኝ ብላ ትቀበላታለች እንጂ ፈጽማ አትረሳውም።

ገረዳችን አሰለፈች በማለዳ ተነሥታ የመኝታ ቤታችንን በር ቆርቁራ ቁልፉን ትቀበልና በላይነሽ እስክትነሣ ድረስ ቡና አፍልታ ቁርስ አሰናድታ ትጠብቃለች።

አንድ ዕለት ማታ ከሥራዬ ገባሁና ከእልፍኝ ቁጭ ከማለቴ በላይነሽ መጣችና ካጠገቤ ቁጭ ብላ «ዛሬ ተጨንቄ ዋልኩልህ» አለችኝ።

«ለምን» ብላት

«አሰለፈች ስታለቅስ ጊዜ»

«ምን ሆና»

«አባትዋ ተመሙባትና በነፍስ ድረሺ የሚል መላክተኛ ተላከባት»

«አባት አላት እንዴ»

«ከላ ልጅዬ ኖርዋታል»

«የት ሀገር? »

«ከአላባ ቁሊቶ»

«ታዲያስ»

«አሁን ልትሔድብኝ ነው»

«እስቲ ጥሪያት» አልኳትና በላይነሽ አሰለፈችን ጠራቻት፤ አሰለፈች እያዘነች መጣችና ከእልፍኝ ግድግዳዋን ተደግፋ ቆመች።

«አባትሽ ታመሙብሽ አሉ» ብላት

«አዎ» አለችኝ ጣቶችዋን በጣቶችዋ እያፍተለተለች፤

«ልጅ ናቸው አርጅተዋል? »

«ያኔ ሲነግሩኝ የግሥጋሴ ጊዜ ነው የተወለድኩት አሉ ይሉ ነበር»

«የመቼው ግሥጋሤ»

«የትግሬ ግሥጋሤ ጊዜ»

«አድዋ»

«ነው መሰለኝ»

«አሁን ምናቸውን ነው የታመሙት»

«እኔ ምን አውቄ - ብቻ በነፍስ ድረሺ አሉኝ፤ ሞተውስ እንደሁ እኔ ምናውቃለሁ አለችና ለማልቀስ ሞካከራት።

«አይዞሽ አታልቅሺ ምናልባት ናፍቀውሽ ቶሎ እንድትሔጂላቸው ይሆናል በነፍስ ድረሽ ያሉሽ»

«አይ አይመስለኝም»

«አሁን አታልቅሺ ዝም በይ» ብላት እያለቀሰች ወደ ጓዳ ሔደች።

ደሞዝዋን ሁሉ ከፈልን ለመሳፈሪያና ለስንቋም በገንዘብ ረዳትና ለመጨረሻ ጊዜ ስንሰነባበት በቅርብ ጊዜ ተመልሳ መጥታ ሥራዋን እንደምትጀምር ነገረችኝ።

ለሊቱን ለበላይነሽ ስለ ገረዳችን ነገርኳት፤ ውሸቷን ነው አልኳት፤ ውሸቷን ላለመሆኑ በላይነሽ ተከራከረችኝ፤ እኔ እርግጠኛ መሆኔን አረጋገጥኩላት፤ ሊነጋጋ ሲል ገረዳችን አሰለፈች የመኝታ ቤታችንን በር አንኳኳች ምነው ብላት ቁልፉን ነው አለችኝ።

«ማታ ዕቃሽን ሁሉ አሰናድተሻልና አንነሳም አልኳት።

«እረስቸው ነበር» አለች

«አይ የቀረው ይቅር ስትመጪ የት ይሔድብሻል»

«ለመንገዴ የሚያስፈልገኝ የሥራ ልብስ ነበር»

«የለበሽውን ለብሰሽ ሒጂ» አልኳት፤ ለጥቂት ጊዜ ድምፅዋን ሳልሰማ ቆየሁ፤ እንደ ገና ደግሞ መዝጊያውን ቆረቆረች፤ ምነው ብላት «ሻሼን እማድቤት ረስቼው ነበርና ቁልፉን ነበር» አለች፤ በላይነሽ ካንገትዋ ገና

አለችና «እባክህ ልስጣት ትውሰደው» አለች አርፈሽ አርፈሽ ተኚ ብዬ ተቆጣኋትና ለአሰለፈች ደምጎ አንነሳም ብዬሻለሁ አልኳት።

ለጥቂት ጊዜ ቆየችና እንደ ገና መዝጊያውን ቆረቆረችና ምነው ብላት «የተዋስኩትን የወይዘሮ ዘቢደሩን ዕቃ መልሼ ልሒድ ብዬ ነው፤ ቁልፉን ነበር» አለች፤ የምን ዕቃ ነው ብላት »መሰለቂያዋን ነው» አለች፤ «በኋላ በላይነሽ ትመልስላታለች፤ አያስቸግርም» አልኳት።

የአሰለፈች መወትወት ስለ እብዛ ከወትሮአችን ይበልጥ ተኝጠን አረፈድን፤ በኋላም በላይነሽ ስትነሣ የማድቤቱን ቁልፍ እንደያዝሁ ተኛሁ፤ በላይነሽ አሰለፈችን ተቆጣቻትና አሰለፈች እያጉረመረመች ሔደች።

ከመኝታዬ ተነሥቼ አሰለፈች ይህን ያህል የተቸገረችበትን በማድቤት ያስቀመጠችውን ዕቃዋን ለማየት ከበላይነሽ ጋር ብንገባ ባንድኒት ቁጭ በሉ ጣሳ ሙሉ ድልህ - ባንድ ከፍ ባለ ጣሳ ሙሉ ቅቤ - በደህና ከረጢት ሁለት ኪሎ ቡና - ባንድ ጨርቅ የተቋጠረ አሥራ አምስት ኪሎ የሚሆን የጤፍ ዱቄት - እንደ ገና ደግሞ በየሥርቻው ስንፈልግ ባንድ ጨርቅ የተቋጠሩ ቅመማ ቅመሞችና ባንድ ጨርቅ የተቋጠረ ሽንኩርት አገኘን።

# ምዕራፍ ፰

«አይሆንም ይህ ለገረዶች ፊት መስጠት አይበጅም፤ እኔ የብዙ ጊዜ ልምድ አለኝ፤ አሁንም ይቺን ልጅ እንደበፊተኞቹ ጐሽ ጐሽ አትበያት» አልኳት ለበላይነሽ።

«ያው ናቸው» አለችኝ በላይነች «ቢያመሰግኗቸው ባያመሰግኗቸው እነሱ እንደ ሆነ ያው መቀነባጠባእውን አይተው፤ ይቺም ደግሞ እስቲ ትሞከራለች፤ ደሞም እኮ ጐሽ ካላሏቸው አይሠሩም አለች።

«እንዳልሽው ይሆናል» አልኳት «የገረዶችን ዓመል ጠንቅቄ አውቃለሁ የሚል ቢኖር ይዋሻል፤ እንደ መልካቸው ነው፤ ብዙ ጠባይ አላቸው፤ ያም ቢሆን አጋማሹንም ቢሆን ማወቁ ይበጃል፤ እንዳልሽውም ሲያመሰግኗቸው ይወዳሉ ይሠራሉም፤ ደሞም አይምሰልሽ በሁሉ ነገር

ስታመሰግኛቸው ትገመቻለሽ፤ በገረዶች ዘንድ መገመትሽም ያቀልሻል፤ በየገባችበት ቤት ሁሉ የወሬዋ መቅድም ታደርግሻለች» አልኳት።

«ነው፤ ያልከውም ይሆናል፤ ግን በደንብ አልገባኝም» አለች «በሁሉ ነገር ጐሽ ጐሽ ብትያት ያለማወቅሽን ታገምቻለለሽ» አልኳት።

«ታዲያ እንዴት ይሁን ትለኛለህ» አለችኝ «ከአቅሟ በላይ አትዘዣት፤ ልትሠራ የምትችለውን ነገር ሁሉ አሠሪያት፤ ብዙ ልብስ ስታጥብ ውላ እንደሆነ ደርበሽ ምጣድ ጣጂ አትበያት ልብሱንም ቢሆን ሳይበዛ አሳጥቢያት እንጂ ባንዴ አትቆልይባት በትንንሹ ያሳጠብሻት እንደ ሆነ ሌላውንም ከበድ ያለ ሥራ ደርባ ልትሠራልሽ ትችላለች።

«አንቺ ሴት ነሽና አንዳንዴ እርጃት ለየጥቃቅኑ ሁሉ እሷን አትፈልጊ፤ በሆነ ባልሆነው ሁሉ አትነዝንዣት፤ ሁለት ቅጣት የለምና ከተቆጣሻት ላጠፋችው፤ ነገር በደሞዝዋ አትቅጫት፤ ዕቃም ብትሰብር ዋጋዋን ከደሞዝዋ እንደትከፍል ንገሪያት።

«በሆድዋ አትበድያት፤ ትብላ፤ ይህን ብልሽም የአበላልዋ ሚዝና ከኛ አበላል እንዲበልጥ አያስፈልግም፤ አንችልም፤ እንዳሻት አትልቀቂያት፤ ሥልጣኑ ያንቺ መሆኑን አሳውቂያት ተቆጣጠሪያት» አልኳት።

በላይነሽ ይዘፍን የነበረውን የቴፐሪኮርድ ክር (ቴፕ) እየለወጠች «እንዲያው ከደምክ እንጂ እነሱ እንደሆነ ቢያባብሏቸውም ቢያበሻቅጧቸውም ያው ናቸው» አለች።

ሐሙስ ዕለት መሰንበቻውን ስለብሰው የከረምኩትን ልብሴን ለውጬ ወደ ሥራዬ ሄድሁ፤ በመሰንበቻው ኮቴ ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎቼን ወደ ለወጥኩት ኪስ ሳላዛውር ረስቼው ሄሁ።

በሰዓት ስመጣ ኮቴን ካስቀመጥኩበት ቦታ አገኘሁት፤ በውስጡ ያሉትን ዕቃዎች ሳወጣ በኪሴ ውስጥ ከነበሩት አንድ ቅጠል ባለ ሀምሳ ብርና ሦስት ዝርዝር ብሮች መሐል ሃምሳውን ብር አጣሁት።

በላይነሽን ጠርቼ ወስዳ እንደሁ ብጠይቅ ያለመውሰዷን አረጋገጠችልኝ፤ እስተነአካቴው ወደ መኝታ ቤት ፈጽማ ሳትገባ መዋልዋንና

በዝቶባት የነበረውን ሥራዋን ስታከናውን መዋሉዋን ነገረችኝ፤ ያልጋውም አለመነጠፍ ያላየችው በዚህ ምክንያት መሆኑን ነገረችኝ።

ገረዳችንን ብርቅነሽን ጠርቼ «ለምን አልጋውን አላነጠፍሽም» ብላት «ዛሬ በዝቶበን ነበርና ከማድቤት ስንደፋደፍ ፈረደብኝ» አለችኝ «ማን ነበር ከመኝታ ቤት የገባው» ብላት «እኔ ለራሴ ሥራዬን ከመሥራቴ ሌላ ምንም አላየሁም አለችኝ።

እንዳትበረግግና እንዳትጠፋ ብዬ የብሩን ነገር ሳላነሳባት ዝም አልኩ፤ ነዶኛልና ምሳዬን ሳልበላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄድኩ፤ የፖሊስ ጣቢያው ፖሊስ ለዚህ ዓይነቱ ነገር የሚሻሉትን ፖሊሶች ነገረኝና ወደዚያ ሄድሁ።

አመለከትሁ፤ ማመልከቻ ጽፈው ያቅርቡ ተባልኩ ማመልከቻዬን ጽፌ ቀረብሁ፤ መርማሪ ወይም አጣሪ ፖሊስ ታዘዘልኝና ቃል መስጠት ጀመርሁ።

«በኪስዎ የነበረው ስንት ብር ኖርዋል»

«ሃምሳ ሦስት»

«ስንቱ ጠፋ»

«ሃምሳው»

«ስላጠፋፉ የሚያውቁት ነገር አለ»

«የለም»

«ገንዘቡን ለምን በኪስዎ ጥለው ሄዱ»

«እረስቼው ነው»

«እንዴት ገንዘብ ይረሳል»

«አዎ ሊረሳ አይገባውም ነበር ግን ስለ ቸኮልኩ ነው»

«እሺ አሁን ገንዘቡ በምን ዓይነት ዘዴ የሚገኝ ይመስሎታል? »

«ዘዴውማ ከናንተ ነው»

«ደህና፤ ገንዘቡ ከኪስዎ ለመኖሩ ምን ምስክር አሎት»

«ምስክር የለኝም»

«ማስረጃስ»

«የለኝም»

«ለምን እርሶ ይህን ያህል ገንዘብ በኪሶ ያዙ»

«ተከልክሏል እንዴ»

«የለም ምክንያቱን ማወቅ አለብን»

«ምክንያት የለውም ያዝኩ»

«ዕቃ ሊገዙ ካልሆነ ወይም ላንድ ሰው ሊሰጡ ካልሆነ በምን ምክንያት ያዙት»

«ገንዘቤ ነው ኪሴ ነው፤ የራሴን ገንዘብ በራሴ ኪስ አስቀመጥኩት»

«ይሄ አይደለም፤ ይሁን፤ አሁን ተወሰደብኝ የሚሉትን ገንዘብ ማን የወሰደብዎት ይመስልዎታል»

«ገርዴ»

«ማን ትባላለች»

«ብርቅነሽ»

«ብርቅነሽ ማ»

«ያባቷን ስም አላውቅም»

«ያባትዋን ስም ሳያውቁ ነው እንዴ የቀጠሯት»

«እንኳን የአባቷን እሷንስ የት አውቃት ነበር»

«ይሁን - ብርቅነሽን የሚጠረጥሩበት ምን ምክንያት አለዎት»

«በቤቱ ሌላ ሰው የለማ»

«እርሶና ብርቅነሽ ብቻ ናችሁ»

«ሚስቴ አለች»

«ማን ይባላል»

«በላይነሽ»

«ይሔ ጠፋ የሚሉት ብር ከሦስታችሁ መሐል ነዋ የጠፋው»

«አዎ»

«ታዲያ ገረድዎ ለመስረቅዋ ምን ማስረጃ አለ»

«ሠረቀቻ»

«አይደለም - ለመስረቋ ማስረጃ ያስፈልጋል»

«ማስረጃማ ካለ እኔው እይዛታለሁ»

«እንደሱ አይደለም - አዩት አድን መጨበጫ ያስፈልጋል»

«መጨበጫውማ በቤቱ ያለችው እሷው ነች»

«ባለቤትዎስ አሉ አይደለ»

«ሚስቴ ሠረቀች ለማለት ነው»

«ማን ያውቃል»

«አይሆንማ የገዛ ገንዘብዋን»

«አሁን ታዲያ በምን ዓይነት ዘዴ ገንዘብዎን ልናስገኝሎት የምንችል ይመስሎታል።»

«መርምሯታ??

«ማንን»

«ብርቅነሽን»

«ምን ብለን»

«ወስደሻል ወይ ነዋ»

«እርሶ ገንዘቡን በኪስዎ አላስቀመጡት እንደሆንስ»

«አስቀምጫለሁ እንጂ»

«ምን ማስረጃ አለዎት»

«መቼም ምሥክር እየቆጠርኩ አላኖር - አስቀምጣጣለሁ አስቀምጣለሁ»

«ይሄ እንዴት ይቻላል»

«ለምን»

«አዩት ምናልባት እርስዎ ገረድዎን ለመጉዳት ብለው ያልጠፋብዎትን ጠፋብኝ ብለው አመልክተው ይሆናል ደሞም እር........

«ለምን ብዬ? ካናደደችኝ አላባርራትም እንዴ»

«ይችላሉ ግን አንዳንድ ሰዎች.......

«ኖ እኔ አንዳንድ ሰዎች አይደለሁማ»

«ያስጨርሱኝ፤ አንዳንድ ሰዎች ቅድም እንዳልኩት ያረጋሉ»

«እኔ አላደርግማ»

«በምን እናውቃለን»

«እንዴ ፖሊሶች ናችኋ»

«ፖሊስ ነቢይ ወይም ወልይ አይደል»

«መሆን አለበት»

«ሆኖ አልተገኘማ»

«ይሔ ስንፍና ነው»

«ማንም ጐበዝ በራሱ ኃይል ነቢይ አልሆነም»

«አሁን በቃ ምንም ተስፋ የለኝ? »

«አለዎት»

«መቼ»

«አይቸኩሉ»

«ገንዘቡ ሳይጠፋ መቸኮ አለብኝ»

«አልጠፋም እንዴ»

«ጠፍቷል»

«ታዲያ ለምን ሳይጠፋ ይላሉ»

«ሳይባክን ሳይመነዘር ማለቴ ነው»

«አይቸኩሉ»

«መቸኰል አለብኝ»

«ለምን»

«ለገንዘቤ»


«ምርመራው ይጣራል»

«መቼ»

«ቀስ ብሎ፤ በብልሃት፤ በዘዴ፤ በመግባባት»

«እንዴት? »

«በመስማማት»



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታችው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

የደራሲው ሥራዎች

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY